# ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

# ሕገ-ኢትዮጵያ (The Ethiopian Constitution)

መግቢያ

**Preamble**

እኛ የኢትዮጵያ ህዝብ በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ አንድ ሰው መብት ድረስ እንዲከበርና እንዲጠበቅ በኢትዮድያ ውስጥ ተጠያቂ መንግስት ለመፍጠር፣ በሕግ የመንግስትን አካል ለመቆጣጠር፣ የመንግስት አካል ወንጀል ከፈፀመ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ በሕግ ለመቅጣትና ከሥልጣናቸው ለማሰናበት፤ በኢትዮድያ ውስጥ መከላከያና ደህንነት ነፃና ገለልተኛ አካል ለማድረግ፣ በሕዝብ ምርጫ ባለሙሉ ሥልጣን ነፃ ተቋማት በፌደራልና በክፍላተ ሀገር ደረጃ ለመገንባት፣ እንዲሁም ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በእኩልነት ተከብሮና የሕግ ልእልና ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍ የመንፈስና የሞራል ነጻነት አግኝቶ ኢትዮድያዊ ዜጋ ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መብት እንዲጎናፀፍ ፣ እንዲሁም ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ፣ እኮኖሚያዊ፣ የጋራ ተጠቃምነታችን ለማረጋገጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ቃል ኪዳን አሰፈላጊነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ የጋራ ሰነድ መሆኑን ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡

በሕገ-ኢትዮጵያ ከመንግስት የበላይነት የሕግና የሕዝብ የበላይነት ተቀዳሚ ይሆናል፡፡ ሕገ ኢትዮጵያ የነጻነታችን ዋስትና የፍትህ የእኩልነት የአንድነታችን የሉዓላዊነታችን ማረጋገጫ የፍትህ ራስ የማዕዘን መሠረት ሆኖ ማህበራዊ ፖለቲካዊ እኮኖሚያዊ ተጠቃምነት ያረጋግጣል፡፡ ይህንን የህግ የበላይነት ሰነድ ሕገ-ኢትዮጵያን በኢትዮጵያ ህዝብ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጽፈን ለእኛና ለሚመጣው ትውልድ የፍትሕ ሰነድ ሆኖ ለዘለዓለም እንዲያገለግል በመስከረም 1,2009 ተፃፈ።

የኢትዮጵያ የሕግ በላይነት ሥርዓት <u>ሕገ-ኢትዮጵያ</u> ተብሎ ይጠራል።

ሕገ-ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መንግሥት መመዘኛ መሠረት ለሕዝባችን 9 ዋና ዋና ጥቅሞችን ያስገኛል።

1) መንግሥት ከሕዝብ በታች ፤ ሕዝብ ከመንግሥት በላይ እንዲሆን ያደርጋል።
2) የመንግሥት ምዝበራንና ሥርዓት አልበኝነት የእኮኖሚ ብክነት የሕዝብና የሀገር ዘረፋ ወንጀሎችን በሕጌ ኢትዮጵያ ይቆጣጠራል፡፡ የአገራችንን ሕዝብ የኢኮኖሚ ተጠቃምነት ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ዜጋ የሥራ ፈጠሪና አምራች ዜጋ እንዲሆን በሕግ ማእቀፍ የሕግ ሥርዓት ይመቻቻል፡፡
3) መንግሥት የሚሠራውን ሁሉ ለሕዝብ በግልጽ የማሳወቅ የሕግ ግዴታ ይጥላል፡፡በሕገ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት የሚሠራዉን ማንኛዉም የሥራ ተግባር የማወቅ መብቱን በሕግ የተከበረ ይሆናል፡፡
4) መሠረታዊ የሕዝብ ነፃነት እስከ አንድ ሰው መብት ድረስ በሕግና በሕግ ብቻ ይከበራል፡፡እንዲሁም የፖለቲካ እና የእኮኖሚ መብቶች በሕግ አግባብ ተጠቃም ይሆናል፡፡
5) ማንኛውም ወንጀል፣ የፖለቲካ ወንጀልን ጨምሮ በአገራችን ውስጥ የሕዝቡ ሠላምና ፀጥታ የሚያውክ ጉዳይ እንዳይኖር የግጭት አፈታት ማለትም በባህላዊና በዘመናዊ በሕግ ሥርዓት ዳኝነት እንዲያገኝ ሲሆን በሕዝብ መካከል ብሄራዊ መግባባት እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡
6) ከሕግ አግባብ ዉጭ የመንግሥት ተፅዕኖ በሕዝቡ ላይ እንዳይደርስ ሕገ ኢትዮጵያ ይከለክላል።
7) ሁሉም ሰው በሕግ ፊት በእኩልነት ትክክለኛ ፍርድ ያለ አድሎአዊ በእኩልነት እንዲያገኝ ያደርጋል።
8) የወንጀል ምርመራ አግባብ ባለው ምርምር እንጂ በቶርች፣ በግርፋት፣በስቃይ ቃል መቀበል እና ቃል መስጠት በሕጌ ኢትዮጵያ የተከለከለ ይሆናል፡፡በሌላ አካልን በግርፋት በሰቃይ የተገኘ የወንጀል ምርመራ በሕገ ኢትዮጵያ ወድቅ ይሆናል፡፡ማንኛዉም ዜጋ ምንም ዓይነት በሰውነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ይከለክላል።
9) ማንኛውም ሰው ፍርዱን በሰውር ሳይሆን በግልጽ በሆነ ፍታዊ ዳኝነት በበቂ መረጃና፣በምስክሮች መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ስለሆነም ሕጋዊ ፍርድ ሕግን ተላላፎ በተገኘዉ አካል ላይ ተፈጻም ይሆናል፡፡

ሀ/ አድሎአዊነት የዳኝነት አሠራር ይቀራል፣

ለ/ በዜጎች መካከል መድሎና መገልል መፈጸም ይቀራል፣

ሐ/ በፍርድ ቤት አሠራር ጣልቃ ገብነት ይቀራል፣

መ/ ፍርድን ማዛባት የዳኝነት ሥርዓት ማጉደል ይቀራል።

ሥ/ የሀገር ሉዓላዊነት እና ብሄራዊ የአንድነት እሴት የምሽረሰሩ ድርግቶች ተሳተፎ መገኘት የሚያስጠይቁ ወንጀሎች ስለሆኑ ሕገ ኢትዮድያ በጥብቅ ይከለክላል።

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

ሕዝብ

1) የበላይ ሕግ፣ ሕገ ኢትዮድያ የሕዝብ ነው።
2) የበታች ሕግ፣ ሕገ መንግሥት፣ መንግስት የሚያወጣው የሥራ ሕጎች ናቸው።
3) የበላይ ሕግ ፐሬዝዳንትን ጨምሮ አገሪቷን የሚገዛ፣ ሕዝቡን በዕኩልነት የሚመራ የአገሪቷ ገዥ ነው። ወይም የአገሪቷ መሪ ነው።
4) የሕዝብን ሕግ፣ ሕገ ኢትዮድያን ድንበር ተላልፎ የሕዝብ ምክር ቤትና የክፍላተ ሀገር ምክር ቤት ሌላ ሕግ ማውጣት የፌደራል መንግሥት ወንጀል ነው። የኢትዮድያ የፌዴራል መንግስት ወንጀል የሕግ የበላይነት ጥሰት ወንጀል ስለሆነ ቅጣቱ መነሻው ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ነው።።
5) የሕዝብ ሕግ፣ ሕገ ኢትዮድያ መቀነስ ስለማይቻል መጨመርና ማሻሻል የሚችልው በድምፅ ብልጫ የኢትዮድያ ሕዝብ ብቻ ነው።
6) ሕገ መንግሥት መቀነስና መጨመር ስለሚቻል ማውጣትና ማሻሻል የሚችለው የፌደራልና የክፍላተ ሀገር ምክር ቤት ብቻ ናቸው።
7) የሕዝብ ሕግ፣ ሕገ ኢትዮድያ አስፈጻሚ አካል፣ ወይም ከመንግሥት ነፃና ገለልተኛ አካል፣ ብሔራዊ የሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት፣ መከላከያና ደህንነት፣ የፌዴራልና የክፍላተ ሀገር ፍርድ **ቤቶች** ፣ የኢትዮድያ ሲቪል ሰርቭስ ኮሚሽን፣ የኢትዮድያ የምርጫ ኮሚሽን፣ የኢትዮድያ ኦዲት ኮሚሽን፣ የኢትዮድያ የሕዝብ ደህንነት ኮሚሽን መሥሪያ ቤቶች ናችው።

<u>ሕገ-ኢትዮጵያ የፌደራል መንግስት መዋቅር!</u>

በሕገ-ኢትዮጵያ የፌደራል መንግስት <u>አስተዳደር ሚዛን ለመጠበቅና ለመቆጣጠር</u> እንዲቻል ዕኩል ስልጣን ያላቸው ሦስት ዋና የመንግስት ቅርንጫፎች አሉት።




ሶስቱ የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት አካላትማዕከላዊ ፤ የሕዝብ ምክር ቤት የሚያወጣቸው የመንግስት ሕጎች አስፈጻሚ አካል፣

1) ፕሬዚዳንት፤
2) ካቢኔዎች

<u>የሕዝብ ምክር ቤት፥</u>

1) ሕግ አውጭና የሕግ መወሰኛ ተብሎ ይጠራል።
2) የሴናተሮች ወለልና የሕዝብ ተወካዮች ወለል ያጠቃልላል።
3) ሁለቱ ወለሎች፣ ሴናተሮችና የሕዝብ ተወካዮች ወለል አንድ ላይ የሚያደርጉት ጉባኤ የሕዝብ ምክር ቤት ጉባኤ ተብሎ ይጠራል።
4) 3 ሴናተሮች ከየ ክፍላተ ሀገር ይመረጣሉ። እንዲሁም፣

5) አንድ ሴናተር ከየአንዳንድ አስተዳዳር ይመረጣሉ።

6) አንድ የሕዝብ ተወካይ ከየአንዳንድ አስተዳዳር ይመረጣሉ።

7) አንድ የሕዝብ ተወካይ ከየአውራጃው ይመረጣል።

ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ፥

1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት! እና

2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት ናቸው።

# አንቀጽ አንድ

# የኢትዮጵያ መንግሥት ስያሜ

1) **ሕገ-ኢትዮጵያ ፌዴራላዊና ክፍላተ ሀገራዊ የመንግሥት አወቃቀር ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚል ሥያሜ ይጠራል፡፡**

2) **ኢትዮጵያ አንዷት ሀገር፣ አንድ ሕዝብ የሚኖርባት ሏዓላዊ ሀገር ናት።**

3) **በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት በድንበር የተከለለ መሬት የለም። ስለሆነም፣ ኢትዮጵያ፣ ሀገር የጋራ፣ ሐይማኖት፣ የግል በሚል መርህ ላይ የተመሠረተች ዜጎቿም በየትኛውም ክፍለ ሀገር በፈለጉበት ሥፍራ መርጠው የመኖር፣ የመሥራት፣ የመነገድ፣ የመማር፣ የመምረጥ፣ እና የመመረጥ ሙሉ መብት አላቸው።**

4) **አድሱ የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት፣ ሕገ ኢትዮጵያ፣ ወይም የበላይ ሕግ ወይም፣ ሏአላዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕግ፣ ወይም፣ የኢትዮጵያ ኮንስትቱሽን ተብሎ ይጠራል።**

5) **ኢትዮጵያ በዓለም አቀፋዊ መተዳደርያ ሥርዓት መሠረት ሁለት መሠረታዊ መተዳደርያ ሕጎች አሏት።**

**ሀ) የሕዝብ ሕግ፥ ሕገ ኢትዮጵያ፣ ወይም ሏአላዊ የአገር ሕግ፣ ወይም የአገሪቱ የሕግ የበላይነት፣ ወይም ኮንስትቱሽን ተብሎ ይጠራል።**

**ለ) የመንግሥት ሕግ፣ ፓርላማ ወይም ሕግ አውጭ ወይም የሕዝብ ምክር ቤት የሚያወጣ ሕግ፣ ሕገ መንግስት፣ ወይም የበታች ሕግ ፣ ወይም ሏአላዊ ያልሆነ የመንግስት ሕግ ተብሎ ይጠራል። ምክንያቱም መንግስት ሏአላዊ አይደለም። መንግስት ማለት ሕዝብን ለማገልገል ሕዝብ የፈጠረውና ሕዝብ የቀጠረው አካል ብቻ ነው።**

# አንቀጽ ሁለት:

# የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን

1) ኢትዮጵያ አንዷት ሏዓላዊት አገር ናት።
2) ሏዓላዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገር ውስጥና ከአገራቸው ውጭ በተለያዩ አገሮች ላይ የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ያጠቃልላል።
3) የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌዴራሉን ክፍላተ ሀገር ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የተወሰነው ነው፡፡
4) ኢትዮጵያ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ከ3-14 ዲግሪ ሰሜን እና ከ33-48 ዲግሪ ምሥራቅ የምትገኝ አገር ስትሆን የቆዳ ስፋቱዋም 1,127,127 እስኳር ካሬ ኪ.ሜ. ነው። በሰሜን ከኤርትራ፣ በምዕራብ ደቡብ ሱዳንና፣ ከሱዳን፣ በደቡብ ከኬኒያ፣ እንዲሁም በምሥራቅ ከጅቡቲ እና ከሶማሊያ ጋር ትዋሰናለች።
5) በታህሣሥ 2, 1950 ዓ/ም ላይ የአሰብ ወደብ የኢትዮድያ ሎአላዊ ወደብ እንደሆነ በዩናይትድ ኔሽን ሪዞሉሽን በአንቀጽ 390V ላይ ተደንግጓል። ስለዚህ የአሰብ ወደብ የኢትዮድያ ሎአላዊ ወደብ ነው።

6) *ኢትዮጵያ በ*UN *ውሳኔ አንቀጽ እ/አ* 390 V, On December 2, 1950 *መሠረት* ***ኤርትራ*** *ከኢትዮጵያ ጋር በሠላም በፌዴረሽን አብሮ ለመኖር ከተሰማማች፥ ኢትዮጵያ በ*UN *ውሳኔ መሠረት ምንም ሣይቀየር የመቀበል ግዴታ አለባት።*

7) *ኢትዮጵያ ከአሜርካ ጋር ያላትን የቆየ ወዳጅነት፣ ቀይ ባሕር ወታደራዊ አንድነት፣ የዳሕላክ ዴሰቶቻችንን አብሮ የመጠቀም፣ ማንኛውም የንግድ፣ የኢኮኖሚ፣እና፣ ወታደራዊ ስምምነቶቻችን ከ* 1903—1973 *ያሉት በሙሉ በሥራ ላይ ለማዋል ኢትዮጵያ በትጋት መሥራት አለባት።*

## *ማብራሪያ፥*

በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ዩናትድ ኔሽን ያፀደቃቸውን ሕጎችና ውሳኔዎች ለመሻር የሚችለው ወይም ሙሉ ስልጣን ያለው አካል በዚህ ዓለም ላይ ራሱ ዩናትድ ኔሽን ጠቅላላ ጉባኤ ብቻ ነው። ስለሆነም፣ ኤርትራም ሆነ ኢትዮጵያ የዩናይትድ ኔሽንን ውሳኔ ለመሻር ምንም ዓይነት ሥልጣን የላቸውም። ስለዚህ በታህሣሥ 2, 1950 ዓ/ም ላይ የአሰብ ወደብ የኢትዮጵያ ሉአላዊ ወደብ እንደሆነ በዩናይትድ ኔሽን ሪዞሉሽን በአንቀጽ 390V ላይ የአሰብን ወደብ የኢትዮጵያ ነው  በማለት ያፀደቀውና የደነገገው የዩናይትድ ኔሽን ጠቅላላ ጉባኤ ነው። ዩናይትድ ኔሽን በታህሳስ 2, 1950 ዓ/ም ላይ የአሰብ ወደብ የኢትዮጵያ ነው ብሎ በሪዞሉሽን 390V ያፀደቀበት ዋና አብይ ነጥቦች በሚከተሉት ላይ ተመርኩዞ ነው። ሀ) የአሰብ ወደብ በታሪክ ለብዙ ሺ ዓመታት የኢትዮጵያ የባሕር በር መውጫዋ መሆኑ ስለተረጋገጠ። ለ) በዩናይትድ ኔሽን መመሪያ መሠረት ማንኛውም ሀገር ከባሕር ጠረፍ በ60 ኪሎ ሜትር ላይ ከተገኘ የግድ የባሕር መውጫ በር የማግኘት ሙሉ መብት አለው ተብሎ የተደነገገ ዓለም አቀፋዊ ሕግ ስለሆነ። ሐ) በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት፣ ኢትዮጵያ ከባሕር ጠረፍ በ60 ኪሎሜትር ላይ የሚትገኝ ሀገር መሆኑ ስለተረጋገጠ ። መ) የአሰብ የባሕር በር ለኢትዮጵያ ሏአላዊ ወደቧ ብቻ ሳይሆን ለዕድገትና ለደህንነቷ ወሳኝ መውጫዋ በር መሆኑ ስለተረጋገጠ።

በዚህ ዓይነት የአሰብን ወደብ ሕዋሃት የትግራይን ክፍለ ሀገር ለመገንጠል ባላቸው ስውር ደባ መሰረት በግፍ ኢትዮጵያን የባሕር በር አልባ አገር ሆና እስከ ዛሬ ድረስ እንድትቆይ አድርጋለች። ይሁን እንጂ፣ ሕገ ኢትዮጵያ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ በሪፈሬንደም ከፀደቀ ዕለት ጀምሮ፤ ኢትዮጵያ የዳህላክ ዴሰቶችን ጨምሮ የአሰብ ወደብ ባለቤት መሆኖን ለዓለም በይፋ ታረጋግጣለች። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ድንበር በUnited Nation Resolution Nu. 390V ላይ ብቻ የፀና ይሆናል። የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ድንበር በLeague of nations 1948 ዓ/ም ላይ እያንዳንዱ አባል አገሮች ካርታቸውን ለUN እንዲያስመዘግቡ ዩናይትድ ኔሽን ባዘዘው መጠይቅ መሠረት ኢትዮጵያ ሕጋዊ ካርታዋን ባስመዘገበችው መሠረት ብቻ የፀና ይሆናል።

## አንቀጽ ሦስት

### የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

**የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሐል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በመሐሉ ምንም አርማ የለውም። ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው አግድም ይቀመጣሉ፡፡**



**አረንጓዴ ቀለም፣ የአገራችን ልምላሜ፣ ተራሮቻችንን፣ ሐይቆቻችንን፣ እና ወንዞቻችንን ይወክላል።**

**ቢጫ ቀለም፣ የአገራችን ተስፋ፣ ዕኩልነት፣ ሰላም፣ የኃይማኖት አገር፣ የክርስትያንና የሙስሊም አንድነትና መከባበር ይወክላል።**

**ቀይ ቀለም፣ የአባቶቻችን ጀግንነት፣ አባቶቻችን ለአገራችን ስለከፈሉት የደም መስዋዕትነት ይወክላል።**

## አንቀጽ አራት

### የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች

1) ለኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት የምርጫ አፈጻጸም ሕግ፣ "አንድ ድምፅ ለአንድ ሰው" በሚለው መርሆ መሠረት ብቻ ይከናወናል።
2) የኢትዮድያ ሕዝብ የሕግ የበላይነት ሕገ ኢትዮድያን በሪፈሬንደም ካፀደቀ ቀን ጀምሮ

የኢትዮድያ ሕዝብ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንትን በድምፅ ለመምረጥ ሙሉ መብታቸው የተጠበቀ ነው። በሕገ ኢትዮጵያ፣በፍርድ ፊት ፕሬዚዳንትን ጨምሮ ሁሉም ኢትዮድያዊ እኩል ነው።

3) ለኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት በአንቀጽ 39 ላይ ከተጠቀሱት ከ3 ከመንግስት ፓርቲዎች መካከል ተወዳድሮ በችሎታው ያሸነፈ ወይም ያሸነፈች ግለሰብ ብቻ ይሆናል ወይም ትሆናለች። ማንኛውም ለፕሬዚዳንትነት ውድድር መቅረብ የሚፈልግ ሰው ከፌዴራል ፓርቲ (ፌፓ) ወይም ከዴሞክራቲክ ፓርቲ (ዴፓ) ወይም ከሪፓብልክ ፓርቲ (ሪፓ) መካከል ተወዳድሮ በችሎታው ያሸነፈ ወይም ያሸነፈች ግለሰብ ብቻ ይሆናል ወይም ትሆናለች።ከዚህ ውጭ የሚመጣ ግለሰብ ወይም ፓርቲ ለኢትዮጵያ ፕሬዚደንት ለመወዳደር እንደማይችሉ መስፈርቱ በጥብቅ ይከለክላል።
4) የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ለመሆን የጾታ ገደብ የለውም።
5) የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ሴትም ሆነ ወንድ የዕድሜ መነሻ ከ35 ዓመት በላይ ሆኖ በአባቱም በእናቱም ኢትዮጵያዊ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በውጭ አገር ላይ የተወለደ ወይም የተወለደች መሆን አለባት።
6) በሕገ ኢትዮጵያ የኤሌክትሮ ኮሌጅ ድምፅ ቆጠራ ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

ሀ/ ኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገርቱን ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ያለምንም ኤሌክትሮ ኮሌጅ ቆጠራ በቀጥታ በሕዝባዊ ድምፅ ብልጫ ብቻ ያሸነፈውን ይመርጣል።

7) በሕገ ኢትዮጵያ ፕሬዚዳንቱን ጨምሮ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከሕገ ኢትዮጵያ በታች ነው ወይም ናት።

8) የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ የመቃወም መብት የለውም ማንኛውም የፕሬዚዳንትን ተቃውሞ የሕዝብ ምክር ቤት በድምጽ ብልጫ ውድቅ ማድረግ ይችላል።

9) በሕገ ኢትዮድያ ማንኛውም ኢትዮድያዊ በሕዝብ ተመርጦ ለሕዝባዊ አገልግሎት ተሰማርቶ፣ ለፌዴራልም ሆነ፣ ለክፍላተ ሀገር፣ ፕሬዝዳንት ሆነ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ለሴነተር ሆነ፣ ለሕዝብ ተወካይ፣ በሲቭልም ሆነ፣ በመከላከያ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በአገልግሎታቸው ዘመን ወንጀል ፈጽመው ከሆነ፣ ወንጀሉ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ማንኛውም አገልጋይ፣ ተመልሶ ለሕዝብ አገልግሎት፣ ከላይ ለተዘረዘሩት ለማንኛውም አገልግሎቶች ለመሳተፍ እንደገና ለመፎካከር መመዝገብ በፍጹም አችልም።

10) ፕሬዚዳንቱ በስልጣን ከባለገ መጀመሪያ ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርባል፤ ወይም ትቀርባለች፤ ቀጥሎ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ ይሰናበታል/ትሰናበታለች።

<u>የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

1) የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት የአገሪቱ የፌደራል መንግስት መሪ ነው። የሕዝብ ምክር ቤት የሚያወጣቸው ሕጎች አስፈጻሚ አካል ነው።
2) የኢትዮድያ ፕሬዚዳንት ከሕገ-ኢትዮጵያ በታች ነው።
3) ለሕገ ኢትዮጵያ በመታዘዝ በታማኝነት ያገለግላል ።
4) የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ለ4ዓመት አገልግሎት ብቻ ይመረጣል። ይሁንና ለሁለተኛ ጊዜ መወዳዳር ይችላል።
5) የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ከሁለት ጊዜ በላይ እንዲወዳደር ሕገ-ኢትዮጵያ አይፈቅድም።
6) ፕሬዚዳንት ምንም ዓይነት ጦርነት ማወጅ አይችልም፡፡ ነገር ግን ጦርነት ማወጅ የሚችለው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ነው።

<u>ምክትል ፐሬዚዳንት</u>

1) ምክትል ፐሬዚዳንት ዕጩ የሚመርጠው ፐሬዚዳንቱ ነው። ነገር ግን የሚያጽድቀው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው።
2) የሀገሩ ፐሬዚዳንቱ በድንገት ከሞተ ወይም ከሞተች ወዲያውኑ ምክትል ፐሬዚዳንት የኢትዮጵያ ፐሬዚዳንት ይሆናል ወይም ትሆናለች።
3) ም/ፐሬዚዳንቱ በስልጣን ከባለገ መጀመሪያ ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርባል፤ ወይም ትቀርባለች፤ ቀጥሎ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ ይሰናበታል/ትሰናበታለች።
4) ፐሬዚዳንቱና ም/ፐሬዚዳንቱ በድንገት ቢሞቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በጊዚያዊነት ሀገሪቷን ይመራል።

<u>የክፍለ ሀገር ዋና አስተዳደር</u>

1) የክፍለ ሀገር ዋና አስተዳደር ከሕገ-ኢትዮጵያ በታች ነው፣ እና የመጀመሪያ ድግሪ ያለው ወይም ያላት መሆን አለበት።
2) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ከፍተኛ የሥራ ኃላፍነት ያለበት ተመራጭ ነው ወይም ነች።
3) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር የጾታ ልዩነት አይገድበውም።
4) የክፍለ ሀገሩዋና አስተዳደር የዕድሜ መነሻ 35 ዓመት እና ከዛ በላይ መሆን አለበት።
5) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር መሆን የሚችለው የክፍለ ሀገሩ ተወላጅ ወይም ከሁለት ዓመት በላይ የክፍለ ሀገሩ ነዋሪ የሆነ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ የሚያውቅ ፣ መሆን አለበት/ባት።
6) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር የሥራ ድርሻ/ አብዘኛውን የክፍለ ሀገሩ ሕግ ይወስናል።
7) ከሕገ-ኢትዮጵያ በታች ክፍለ ሀገሩ ለሚያወጣው ሕግ በመታዝዝ በታማኝነት ክፍለ ሀገሩን ለ4 አመት ያገለግላል።
8) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ለ4 አመት አገልግሎት ብቻ ይመረጣል፡፡ነገር ግን ለሁለተኛ ጊዜ መወዳደር ይችላል።
9) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ለ3ኛ ጊዜ እንዲወዳደር ሕገ ኢትዮጵያ አይፈቅድም።
10) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር የክፍለ ሀገሩ ምክር ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ የመቃወም መብት የለውም ፡፡ ማንኛውም የፐሬዚዳንትን ተቃውሞ የክፍለ ሀገሩ ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ ተቃዉሞውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።

11) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር በድንገት ከሞተ ወይም ከሞተች ወዲያውኑ ምክትል አስተዳደር የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ይሆናል ወይም ትሆናለች።

12) የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር በስልጣን ከባለገ መጀመሪያ ወደ ክፍለ ሀገሩ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርባል ወይም ትቀርባለች ቀጥሎ የክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ ያሰናብቱታል።

<u>የክፍለ ሀገሩ ምክትል አስተዳደር</u>

እጩውን የሚመርጠው የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳደር ነው፡፡ነገር ግን የሚያጸድቀው የክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ምክር ቤት ይሆናል።

# <u>አንቀጽ አምስት</u>

<u>ፌዴራል ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ የሕግ አስፈጻሚና የሕግ ተርጓሚ መንግስት አካል፤</u>

1. የፍትህ ሥርዓት ዉስጥ የሕግ ሙያ ብቃትና ችሎታ ባሌበት በሕዝብ ዘንድ ታማኝነት ያላቸው በሕዝብ የተመረጡ ሳባት (7) ዳኞች ይኖሩታል። እነዚህ ሰባቱ ዳኞች ከማንኛውም ፓርቲ ነፃ የሆኑ መሆን አለባቸው።
2. በተለይም በአንቅጽ 39 የተደነገጉ ፓርቲዎች:

   ሀ) ፌዴራል ፓርቲ (ፌፓ)

   ለ) ዴሞክራትክ ፓርቲ (ዴፓ)

   ሐ) ሪፓብልክ ፓርቲ (ሪፓ) ነፃ የሆኑ መሆን አለባቸው።
3. የኢትዮጵያ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዋና ጽሕፈት ቤት በኢትዮጵያ ዋና ከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ይሆናል።
4. የኢትዮጵያ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከ14ቱ ክፍላተ ሀገሮች የሚመጡትን የይግባኝ ውሳኔዎች ላይ የመጨረሻ ፍርድ ይወስናል።
5. የኢትዮጵያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች የአገልግሎት ዘመናቸው 6 አመት ብቻ ይሆናል፣ ነገር ግን በየ 6 ዓመት በአገራዊ ምርጫ ላይ እንደገና መወዳደር ይችላሉ። የኢትዮጵያ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በየ6 ዓመት እንደገና ለመመረጥ የጊዜ ገደብ የለባቸውም ።

6. የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ፍርድ ቤት ዳኞች የአገልግሎት ዘመናቸው 4 አመት ብቻ ይሆናል፣ነገር ግን በየ4 ዓመት በየክፍለ ሀገር ምርጫ ላይ እንደገና መወዳደር ይችላሉ። የክፍለ ሀገር ዳኞች በየ4 አመት እንደገና ለመመረጥ የጊዜ ገደብ የለባቸውም።
7. የክፍለ ሀገር የኢትዮጵያ ፌዴራል ሕጎች በሕገ-ኢትዮጵያ ሥር ሆነው እንደ ክፍለ ሀገሩ ሕጎች ይለያያሉ።
8. የኢትዮድያ የክፍለ ሀገር ፌዴራል ዳኞች የሥራ ድርሻ አብዘኛውን የክፍለ ሀገሩ ሕግ ይወስናል።

አንቀጽ ስድሰት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር የህገ-ኢትዮጵያን ዓላማዎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ በዴሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት፣እንዲሁም የወደፊት የጋራ ዕድላቸውን የሚያንጸባርቅ ሆኖ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ ሳባት

## ስለ ቋንቋ

1) ማናቸውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በእኩልነት የመንግሥት እውቅና ይኖራቸዋል፡፡
2) አማርኛ የፌዴራሉ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ የሥራ ቋንቋ ይሆናል፡፡

አንቀጽ ስምንት

ስለ ዜግነት

1) ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ የሆነ ግለሰብ ከወላጆቹ/ከወላጆቿ አንደኛቸው ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/የሆነች የኢትዮጵያ ዜጋ የመሆን መብቱ ይጠበቅበታል፡፡
2) ማንኛውም ግለሰብ ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/የሆነች የሁለት አገር ዜጋ የመሆን ሙሉ መብት አለው/አላት።

3) የውጭ ሀገር ዜጐች የኢትዮጵያ ዜግነት ከጠየቁ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ዜግነትን በሚመለከት ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

4) ማንኛውም ሰው ነጭም ሆነ ጥቁር በኢትዮጵያ ሀገር ላይ የተወለደ ሁሉ

ያለ አንዳች ጥያቄ ኢትዮጵያዊ ነው/ነች ፤ወይም የኢትዮጵያ ሙሉ ዜጋ ነው/ነች፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>አንቀጽ ዘጠኝ</u>

<u>የሕገ-ኢትዮጵያ መሰረታዊ መርሆዎችና የሕዝብ ሉዓላዊነት</u>

1) ሕገ-ኢትዮጵያ ሁሉንም የነፃነት መብት፣ የኢትዮድያ ሕዝብ ሥልጣን በላይነት፣ የኢትዮድያ ልዑላዊነት የመጠብቅ ኃላፊነት፣ ከአገራችን ላይ የዜር በሽታ አስወግዶ የሕዝባችን አንድነት ለመጠበቅ የበላይ ሥልጣን ያለው፣ ከመንግስት በላይ ለኢትዮድያ ሕዝብ ሙሉ የሏአላዊነት ስልጣን የሰጠና፣ ያረጋገጠ፣ የኢትዮድያ የላዕላይ ሪዕሴ ሕግ ነው።

2) ሕገ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመንግስት በላይ ያለው ነጻነትና የሴትና የወንድ እኩልነት ማረጋገጫ ነው።

3) የኢትዮጵያ ሕዝብ የሕግ የበላይነት መብቱን የምጠብቀው በተመረጡ ተወካዮቹ አማካይነት፣ ወይም ሕዝቡ በቀጥታ በመሳተፍ ነፃነቱን ይጠብቃል።

<u>አንቀጽ አስር</u>

<u>የሕገ-ኢትዮጵያ በላይነት</u>

1) ሕገ-ኢትዮጵያ የሀገርቱ የበላይ ወይም የላዕላይ ሪዕሴ ሕግ ነው።

2) የኢትዮድያ ሕዝብ በብሔራዊ ሪፈረንደም የሕግ የበላይነት ሕገ ኢትዮድያን ካፀደቀ ቀን ጀምሮ የሕገ መንግስትና፣ የሕግ የበላይነት ሕገ ኢትዮድያ ሥልጣን የተለያየ ይሆናል።

3) የሕግ የበላይነት ሕገ ኢትዮድያ የበላይ ሕግ ስለሆነ፣ የሚያፀድቀውም የሚያሻሽለውም ባለቤቱ የኢትዮድያ ሕዝብ ብቻ ይሆናል።

4) ሕገ መንግሥት የበታች ሕግ ስለሆነ፣ የሚያፀድቀውም የሚያሻሽለውም ባለቤቱ የኢትዮድያ መንግሥት የሕዝብ ምክር ቤት ብቻ ይሆናል።

5) ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕግ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

6) ማንኛውም ዜጋ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት፣ እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕግን የማስከበርና ለሕግ ተገዢ የመሆን ግዴታ አለባቸው፡፡
7) በዚህ ሕግ ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡
8) ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው፡፡

<u>አንቀጽ አስራ አንድ</u>

<u>የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች</u>

1) ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፡፡
2) የማንኛውም ዜጋ የግልና የቡድን ሰብዓዊና የዲሞክራሲ መብቱ የተከበረ ነው።
3) በሕገ ኢትዮጵያ ጠጥቶ ማሽከርከር ፈጽሞ የተከለከለ መብት ነው።

<u>አንቀጽ አስራ ሁለት</u>

<u>የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት</u>

1) መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡

መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡ መንግሥት በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ሐይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

<u>አንቀጽ አስራ ሦስት</u>

<u>የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት</u>

1) የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡
2) ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት ይችላል፡፡ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>አንቀጽ አስራ አራት</u>

## <u>የአካል ደህንነትና ነጻነት መብት</u>

1) የአካል ደህንነትና ነጻነት ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ መብት በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው፡፡ይህ ደግሞ በዓለምአቀፍ ሰብዓዊ መብት አዋጅ ላይ የተደነገገ ነው።

አንቀጽ አስራ አምስት

የሕይወት መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም፡፡

አንቀጽ አስራ ስድስት

የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

አንቀጽ አስራ ሰባት

የነጻነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ወንድም ሆነ ሴት ነጻነቱን/ቷን አያጣም/አታጣም፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

አንቀጽ አስራ ስምንት

ኢሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከል

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም፡፡ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው፡፡

3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታ ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3«በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት»የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፤

ሀ/ ማንኛውም እስረኛ በእስራት ላይ ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ፣ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣ ያከናዉናል፡፡

ለ/ ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፣

ሐ/ የማኅበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት፣

መ/ በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈጸመውን ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ የልማት ሥራ፡፡

<u>አንቀጽ አስራ ዘጠኝ</u>

<u>በሕግ የተያዙ ሰዎች መብት</u>

1) ወንጀል ፈጽመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸውን ክስና ምክንያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው፡፡
2) የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፤የሚሰጡት ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው፡፡
3) የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው፡፡ይህም ጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም፡፡ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው መብት አላቸው፡፡

4) የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜው ገደብ ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዙበትን ምክንያት ካላስረዳ፣ፍርድ ቤቱ የአካላዊ ጉዳት እንዳይደረስባቸዉ በሕግ የመከላከል መብት ያጎናጽፋል፡፡
5) በቤተሰብ የመጠይቅ ሕክምና ጠቤቆቻቸዉ የሐይማኖት መሪዎቻቸዉ የማግኘት ነጻነታቸውን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ መብት ፍርድ ቤቱ ያስከብራል፡፡ እነዚህ መብቶች ሊጣስ የማይችል መብት መሆኑን ያካቲታል፡፡
6) ፍትሕ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ምክንያት ሲያጋጥም ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል፡፡የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የመወሰን ኃላፊ በመሆኑ የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው ወደ ፍርድት ቤት የማቅረብ ግደታ ያካቲታል፡፡
7) ሕግ በማስከበር ረገድ የዜጎች እንግልት ማስቀረት የተቀላጠፈ ሕጋዊ አሠራር እና ደንብ ማስፈጸም ፍርድ ቤት የጊዜና የገንዘብ ብክነት መቆጣጠር ለዜጎች ፍትህ በማጎጽፍ እና በሕግ የተያዙ ዜጎች መብት የሚያስከብር መሆን አለበት፡፡
8) የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም፡፡እንዲሁም በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
9) የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው፡፡ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ</u>

<u>የተከሰሱ ሰዎች መብት</u>

1) የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኃላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው፡፡ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ሕይወት፣የሕዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡
2) ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

3) በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር፣በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው፡፡
4) የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ያቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
5) በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
6) ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡
7) የፍርዱ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጐምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ አንድ</u>

<u>በሕግ በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት</u>

1) በሕግ በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፡፡
2) የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ እና ፍትህ ለማስከበር፣ ከትዳር ጓደኞቻቸው ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሐይማኖት መሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው፣ እና ከሕግ አማካሪዎቻው ጋር ለመገናኘትና እንዲጐበኟቸውም እድል የማግኘት መብት አላቸው፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ ሁለት</u>

<u>የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ</u>

1) ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም፡፡ እንዲሁም ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ ሦስት</u>

በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ አራት</u>

<u>ስለ ቅጣትና ስለመከልከሉ</u>

1) ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ጠጥቶ ማሽከርከር በፌዴራል ሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው።
2) በሕገ-ኢትዮጵያ ማንኛውም ወጣት እድሜው ከ21 ዓመት በታች የሆነ ሁሉ መጠጣትና ማጨስ በፌዴራል ሕግ ወንጀል የሚያስቀጣ ነው።
3) በሕገ-ኢትዮጵያ ልጆች በፈጸሙት ወንጀል ወላጆች ፣ወላጆችም በፈጸሙት ወንጀል ልጆች፣በአጠቃላይ የቤተሰብ አባላት የወንጀሉ ተባባሪዎች እስካልሆኑ ድረስ አይጠየቁም።
4) ማንኛውም የቁማር ዓይነት በአገራችን ውስጥ ፈጽሞ የተከለከለ የኢትዮድያ የፌደራል መንግሥት ወንጀል ነው።

<u>አንቀጽ ሃያ አምስት</u>

<u>የክብርና የመልካም ስም መብት</u>

1) ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር እና የማስከበር መብት አለው፡፡ማንኛውም ሰው የራሱን ስብእና ከሌሎች ዜጐች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የማሳደግ መብት የለውም። ስሆነም ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብዓዊነቱ እዉቅና የማግኘት መብቱ የተደነገጌ ሲሆን እነዚያም ዓለማቀፋዊ ድንጋጌዎች ዉስጥ የተካተቱ የሰዉ ልጅ መብቶችን ጭምር በህገ ኢትዮጵያ ተግባራዊነታቸዉ በሕግ አግባቢ የተረጋገጡ ናቸዉ፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ ስድስት</u>

<u>የእኩልነት መብት</u>

1) ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ ሰባት</u>

<u>የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት</u>

1) ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው፡፡ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል፡፡ነገር ግን ቤቱ የወንጀለኞች ሥራ የሚከናወንበት ሆኖ ከተጠረጠረ፣ ቤቱና ንብረቱ በወንጀል ተግባር በዘረፋና ሙስና በተገኘ ገንዘብ የተሰራ፣ ወይም የባንክ ዕዳ ያልተከፈለበት ከሆነ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊፈተሽ ወይም ሊታገድ ይችላል ።
2) ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውንና የሚጻጻፋቸው በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች እንዲሁም በቴሌፎን በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም፡፡
3) የመንግሥት ባለሥለጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን የሕዝብን ሰላም፣ወንጀልን በመከላከል ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ሕጐች መሰረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችለም፡፡

<u>አንቀጽ ሃያ ስምንት</u>

የሐይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነጻነት

1) ማንኛውም ሰው የማሰብ የሕሊና እና የሐይማኖት ነጻነት አለው፡፡ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሐይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ የመከተል የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፡፡

2) የሐይማኖት ተከታዮች ሐይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የሐይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ፡፡
3) ማንኛውንም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነጻነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፡፡
4) ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሰረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው፡፡
5) ሐይማኖትና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት ሰላምን፣ ጤናን፣ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ፣ የአገራችን ባህል የሚቃረን ከሆነ፣ የሌሎች መሰረታዊ መብቶች የሚቃረን ከሆነ በህግ ይገደባል።

<u>አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ</u>

<u>በሰብእና ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

1) ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጐች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር፣ ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም፡፡
2) የዚህ ዓይነት ወንጀል በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምሕረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም፡፡

ምዕራፍ አራት

ዴሞክራሲያዊ መብቶች

አንቀጽ ሳላሣ

የአመለካከት እና አሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት

1) ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል፡፡
2) ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው፡፡ይህ ነጻነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴዎችን በመጠቀም ብሄራዊ የሕዝብ

ጥቅም በማይጎዳ መልኩ የማሰራጭት መብት ይችላል፡፡ማንኛውንም ዓይነት መረጃ መስጠትና መረጃ መቀበል መብቶችን ያካቲታል፡፡ነገር ግን የሀገር ሉዓላዊነት የሚጎዳ መረጃ ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ በሕግ የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡ እንዲሁም አሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን ሕጋዊ መብቶች ናቸዉ፡፡

3) የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙኃን፣እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነጻነት ተረጋግጧል፡፡ የፕሬስ ነጻነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፡፡

ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

ለ/ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድልን፡፡

4) ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሐሳቦችና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ኘሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነጻነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

5) በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፡፡

6) እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነጻነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጐች ብቻ ይሆናል፡፡የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡የጦር ቅስቃሴዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናል፡፡

7) ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ ሳላሣ አንድ</u>

<u>የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

1) ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ መንግስት መጠንቀቅ አለበት።

<u>አንቀጽ ሳላሣ ሁለት</u>

<u>የመደራጀት መብት</u>

1) ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው፡፡ ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች እና ግለሰቦች! በሕግ የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡

<u>አንቀጽ ሳላሣ ሦስት</u>

የመዘዋወር ነጻነት

1) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነጻነት አለው፡፡
2) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በፈለገዉ ጊዜ ወደ ሀገሩ የመመለስ መብት አለው፡፡
3) ከእንግዲህ በሕግ ወጥ መንገድ ከሀገር መሰደድ እንዲቆም ማንኛውም ኢትዮድያዊ በሕጋዊ መንገድ ከሀገር ወደ ውጭ አገር ሄዶ የመማር፤ የመነገድና፤ የመስራት ሙሉ መብት አለው።
4) ማንኛውም ኢትዮድያዊ ከተወለደ ዕለት ጀምሮ የራሱ ስምና ፓስፖርት በወላጆቹ አማካይነት የግድ ማግኘት አለበት።
5) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እድሜው (አስራ ስምንት) ዓመት ሲሞላው ፓስፖርት በተወለደበት አከባቢ ያለ አንዳች ውጣውረድ የማግኘት ሙሉ መብት አለው።
6) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እድሜው (አስራ ስምንት) ዓመት ሲሞላው ያለ አንዳች የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ፈቃድ ማምልከቻ ሣያስፈልገው፣ በቀጥታ ወደ ፈለገበት አገር ሄዶ የመማር፤ የመነገድና፤ የመስራት ሙሉ መብት አለው።
7) ሴቶች እናቶችና አሣዳጊዎች ለልጆቻቸው ከተወለደበት ዕለት ጀምሮ ዕድሜያቸው (አስራ ስምንት) ዓመት እስኪሞላ ድረስ ፓስፖርት ለማስወጣት ሙሉ መብትና ኃላፍነት አለባቸው።

<u>አንቀጽ ሳላሣ አራት</u>

<u>የዜግነት መብቶች</u>

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ከፈቃዱ/ከፈቃዷ ውጭ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን/ዜግነትዋን ሊገፈፍ ወይም ልትገፈፍ አይችልም/አትችልም፡፡ስለሆነም ኢትዮጵያዊ/ ኢትዮጵያዊት ዜጋ ከሌላ ሀገር ዜጋ ጋር የሚፈጽመው/የምትፈጽመው ጋብቻ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን/ዜግነትዋን አያስቀርም፡፡
2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት በሕግ የሚያስገኘውን መብት ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አለው፡፡ይኼውም በውጭ አገር በመወለድ ወይም በመኖር የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ፈቃድ ሃብትና ንብረት የመያዝ መብታቸው በውጭ አገር የሚኖረውን ገንቢ ሃይል ለማሰባሰብና ፊቱን ወደ አገሩ እንዲመልስ የጣምራ ዜግነት (double nationality) መብት የተጠበቀ ነው።
3. ማንኛውም ዜጋ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን የመለወጥ መብት አለው፡፡
4. ኢትዮጵያ ከአጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማይቃረን መንገድ በሚወጣ ሕግ እና በሚደነገግ ሥርዓት መሰረት የኢትዮጵያ ዜግነት ለውጭ ሀገር ሰዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ ሳላሣ አምስት</u>

<u>የጋብቻ፣የግልና የቤተሰብ መብቶች"</u>

1) በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ስለዚህ በጋብቻ አፈጻጸም በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፡፡ በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር ዘንድ የቤተሰብ ሕገ ድንጋጌዎች ዉስጥ ይደነገጋሉ፡፡
2) ጋብቻ በተጋቢዎች ነጻና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሠረታል፡፡
3) ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው፡፡ከሕብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡
4) የግል እና የቤተሰብ ሐይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጐች መሠረት በሴት ልጅ ላይ የሚደርግ የግርፋት ግፍ፤ በሕገ ኢትዮድያ ፈጽሞ የተከለከሉ ናቸው።
5) በሕገ ኢትዮጵያ ጋብቻ በ1 (በአንድ) ወንድና በ1 (በአንድ) ሴት መካከል የሚደረግ ጥምረት ብቻ ነው።
6) በሕገ- ኢትዮጵያ ጋብቻ ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች መፈፀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።

## የፍቺ ማብራሪያ፥

7) ባልና ሚስት በሚፋቱበት ወቅት፣ ሁለቱም ከጋብቻቸው በፊት በግላቸው ያፈሩትን ሐብት ባልም ሆነ ሚስት፣ የመካፈል መብት የላቸውም።

8) ባልና ሚስት በሚፋቱበት ወቅት፣ ሁለቱም ከጋብቻቸው በኋላ አብሮ ያፈሩትን ኃብት ሁለቱም ዕኩል የመካፈል መብት አላቸው።

## አንቀጽ ሳላሣ ስድስት

## የሴቶች መብት

1) ሴቶች መብቶችና በህግ ጥበቃ ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
2) ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
3) ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት በማህበራዊ በእኮኖሚያዊ በፖለቲካዊ ተሳትፎ ወደ ፊት በሚወጡ ሕገ ድንቦች ተጠቃምነታቸዉ ይረጋገጣል፡፡ስለሆነም ሴቶች የቤተሰብ አስተዳዳር እንዴመሆናቸዉ መጠን በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት መስጠትን ያካቲታል፡፡
4) ሴቶች ከጐጂ ባሕል ተጽዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግሥት ማስከበር አለበት፡፡
5) ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጐች፣ ወጐችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፡፡ እነሱም ከዚህ በታች በንዑስ ቁጥር ከ1 እስከ 10 ተዘርዝረዋል።

1) ሴቶች የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፡፡የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የሕጻኑንና የቤተሰቡን ድህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል፡፡
2) በሕገ ኢትዮጵያ ሴት ልጅ ጠለፋ! አስገድዶ መድፈር! ፈጽሞ የተከለከለ ሲሆን የፌዴራል ሕግ ወንጀል ይሆናል።
3) ሴቶች የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሰረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል፡፡

4) ሴቶች በብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም፣ በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች አሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጠ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
5) በሕገ-ኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዣ በጥብቅ የተከለከለ ነው።
6) ሕገ-ኢትዮጵያን ሕግን በመተላለፈ ሴት ልጁን በሰዉር ግርዠት ያሰፈጸመ የፈጸመ ሰው በወንጀል ሕግ ይጠየቃል፡፡ሕግ በመተላለፍ ደርግቱን ተፈጸሞ የተገኘ እንደሆነ በድርግቱ የፈጸመ ያሰፈጸመ አካል በወንጀል ሕግ (አስር ዓመት) እስራት አምስት ሺህ የኢትዪጵያ ብር ቅጣት መቀበል አለበት።
7) በሕገ ኢትዮጵያ ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይም መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡ስለሆነም ሴቶች የቅጥር የሥራ እድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፡፡
8) ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መርጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው፡፡

**10** የሴት ልጅ በጉልበት የሐይል ሚዛን በመጠቀምና በማስገደድ ከመልካም ፈቃድ ወጭ የሚደረግ ዛቻ የብቀላ መንገዶች እና ዜደዎች በመጠቅም ማንኛውም መርዝ፤ ኬምካል፤ እና አሰድ በሰዉነት ላይ መድፋት የተፈጥሮ አካል ማጉደል፤ ፊት ማበላሸት፤ የወደፊት ሕይወት አካላዊ ጉዳት ማስከትል፤ ወንጀሉ ከባድ የሰዉ ልጅ ክብር የሚያዋርድ ድርግት በመሆኑ፤ በዚህ ዓይነት ወንጅል መሳተፍ በፍርድ ቤት የተረጋገጠባቸው ግለሰቦች በሙሉ፤ የሞት ቅጣት መቀበል አለባቸው።

<u>አንቀጽ ሳላሣ ሳባት</u>

<u>የሕጻናት መብት</u>

ማንኛውም ሕጻን የሚከተሉት መብቶች አሉት፤

1) በሕይወት የመኖር.
2) ስምና ዜግነት የማግኘት.

3) ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት.
4) ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ በትምህርት በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣
5) በትምህርት ቤቶች ወይም በሕጻናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነጻ የመሆን፡፡
6) ወጣት አጥፊዎች፣በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ፣ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግሥት ወይም በግል አካላዊ ጉዳት የደረሰባቸዉ ዜጎች በተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ቅዲሚያ እንክብካቤ ልደረግላቸዉ ሕጉ ያዛል፡፡በሰዉና በተፈጥሮ ሠራቸዉ ምክንያት አካላዊ ጉዳት የደረሰባቸዉ ሕጻናት በማንኛዉም ሥፍራ የተለየ ትኩረትና እገዛ እንዲደረግ ሕገ ኢትዮጵያ ቅዲሚያ ያዛል፡
7) ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕጻናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕጻናት ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ ሕጻናት የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም መልካም ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ደህንነታቸውን እና ትምህርት እንዲያገኙ የሚረዱ ተቋሞች በሕግ እንዲፈጠሩ ሕጋዊ መንገዶችን ያበረታታል፡፡
8) መንግሥት በተፈጥሮ ወይም ሰዉ ሠራስ የአካል ጉዳተኞችን ሕጻናት ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡
9) ከሰዉ ልጅ ከሥነ ምግባር ዉጭ ኢትዮድያዊም ሆነ የውጭ ዜጋ ከሕግና ከሞራል ዝቅተኝነት ሕጻናትን ለግብረ ሥጋ ግኙኙነት መጠቀም ለሦስተኛ አካል ማቀቅረብ ወንድ ወይም ሴት ከእድሜ ክልል በታች ለወስብ መጠቀምያነት መያዝ የወስብ ባርያ ማድረግ ወይም ለዉጭ ዜጋ ማቅረብ ከሕፃናት ጋር ለወስብ መተኛት ለወጭ ዜጋ ለንግድ ማቅረብ በስዉር መጠቀምያነት ያቀረበ/ያቀረበች በሕገ ኢትዮጵያ ወንጀል ተከስሰው በማረጋገጫ ተደርሶባቸው በፍርድ ቤት የተረጋገጠባቸው ግለሰቦች በሙሉ፤ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ፤ ያለ አንዳች ምህረት በኤሌትሪክ ወይም በስቅላት የሞት ቅጣት መቀበል አለባቸው።
10) በሕገ- ኢትዮጵያ ወላጅ ከገዛ ልጁ ወይንም ሕፃናት አሳዳጊዎች በሙሉ፤ ከወንድ ወይም ከሴት ልጁ ጋር በስዉር ወስብ መፈጸም በሕግ የተከለከለ ሲሆን ፣ በዚህ ዓይነት ወንጀል መሳተፍ በፍርድ ቤት የተረጋገጠባቸው ግለሰቦች በሙሉ፤ የሞት ቅጣት መቀበል አለባቸው። በዚህ

ዓይነት ወንጀል ሕጻናት አሳዳጊ እንዳያጡ መንግስት በቂ ትኩረት ስጥቶ አስፈላጊውን እንክንካበ እንድደረግላቸው በቂ በጀት መመደብ አለበት።

11) ማንኛዉም ሕጸናት ላይ የሚፈጸም ማህበራዊ ሞራላዊ ጥቃቶች በትምህር ቤት፤ ቤቴ እምነቶች የሕጸናት ማሳደጊያ ተቋማት በመምህራኖቻቸዉ ወይም በአሳዳጊዎቻቸዉ የምፈጸም የወስብ ባርያ የማድረግ ወንጀል በፍርድ ቤት የተረጋገጠባቸው ግለሰቦች በሙሉ፤ በአደባባይ የሞት ቅጣት መቀበል አለባቸው።

<u>አንቀጽ ሳላሣ ስምንት</u>

ፍትሕ የማግኘት መብት

1) ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ፡፡
2) ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣
3) ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

<u>አንቀጽ ሳላሣ ዘጠኝ</u>

የመምረጥና የመመረጥ መብት

1) በሕገ-ኢትዮጵያ በዘር! ስም መደራጀት የፌደራል መንግሥት ወንጀል ነው። በሕገ-ኢትዮጵያ፤በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ(ሦስት) ቋሚ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ እንዲኖሩ ይፈቅዳል።እነዚህ ፓርቲዎች መሪያቸውን በየ አራት (4) ዓመት ይመርጣሉ።

<u>እነዚህ ፓርቲዎች! ስማቸው እንደሚከተለው ተደንግጓል።</u>

1) ፌዴራል ፓርቲ (ፌፓ)
2) ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ዴፓ)
3) ሪፓብልክ ፓርቲ (ሪፓ) ናቸው።

በሕገ-ኢትዮጵያ መሰረት ለፕሬዚዳንትነት ለመወዳደር የሚችሉት ግለሰቦች የብሔር፤የጎሳ፤ስም በመጠቀም ለመፎካከር አይችሉም።ለምሳሌ አማራ ኦሮሞ ጋምቤላ ወይም ኦጋዴን ወዘተ...በሕገ-ኢትዮጵያ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም! በዘር! በጾታ! በቋንቋ! በሐይማኖት! በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት የመምረጥና የመመረጥ መብቶች አሉት፡፡

1) በቀጥታ እና በነጻነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ!
2) ዕድሜው አሥራ ስምንት (18) ዓመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥ!
3) በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ፡፡ምርጫው ሁሉን ዓቀፍ! በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነጻነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡
4) በፖለቲካ ድርጅቶች! በሠራተኞች! በንግድ! በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በፍላጐቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት፡፡ በዚህ አንቀጽ በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ  ይፈጸማሉ፡፡

<u>አንቀጽ አርባ</u>

የንብረት መብት

<u>በኢትዮጵያ ውስጥ ሀገር የጋራ ነው፣ ሐይማኖት የግል ነው።</u>

1) ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ ይከበርለታል/ ይከበርላታል፡፡ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጐች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ

ንብረትን የማፍራት የመሸጥ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል፡፡ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ «የግል ንብረት» ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው ማኅበራት ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በመፍጠር ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው፡፡

2) የመንግሥት የመሬት ሞኖፖሊ ፖሊስ በህግ የተከለከለ ይሆናል። የመንግሥት የመሬት ሞኖፖሊ ወደ ግለሰብ የመሬት ባለቤትነት ይዛወራል። እንዳስፈላጊነቱ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የራሱ የሆነ የመሬት ዉርስ የመሬት ባለቤት መሬቱን በፈለገው መንገድ የማልማት የማስያዝ የመሸጥና የመለወጥ መብት አለው።በተዘዋዋሪ የግጦሽ መሬት ከብት እያረቡ የሚኖሩ፤ ሥፍራው በተወሰነ ወደ ዘመናዊ የከብት እርባታ ኢኮኖሚ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል።

3) በሕገ-ኢትዮጵያ መሠረት የገጠር መሬት በ14ቱ ክፍለ ሀገራት ውስጥ ለአርሶ አደር የገበሬ ማህበር ብቻ ይደለደላል።

4) በሕገ-ኢትዮጵያ ማንኛውም የትግራይ ነፃ አውጭ (TPLF) ድርጅት ወይም የኢሕአደግ እንዲሁም፣ የብልግፅና ፓርትና መንግስት፣ ከውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ከግለሰቦችም ሆነ ከድርጅት ጋር ያደረጋቸውን የመሬት ሆነ ሌላም ማንኛውም ስምምንቶች እንዲሁም ስለገጠር መሬት ኪራይ በሚመለከት ውሎች በሙሉ ውድቅ ናቸው።

<u>አንቀጽ አርባ አንድ</u>

የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች

1) የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚመራ ሳይሆን፤ በነፃ ገበያ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።እንዴ አስፈላጊነቱ፣መንግሥት የገበያ ኢኮኖሚውን ማረሚያ ፖሊሲዎች ማውጣት ይችላል።

2) ነገር ግን <u>ጤፍ በኩንታል፣ ጋዝ በሊትር፣ ቤቆሎ በኩንታል፣ ሥጋ በኪሎ፣ ወተት</u> <u>በሊትር፣ እና ዜይት በሊትር</u>፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አቅም ጋር በማመዛዘን የዋጋ ተመን ማውጣት የሚችል የኢትዮጵያ ፌደራልና የክፍላተ ሀገር <u>የሕዝብ ምክር ቤት</u> ብቻ ነው።

3) የኢትዮጵያ ክራይ ቤቶች በሙሉ፣ ሕገ ኢትዮጵያ በረፈረንዴም ከፀደቀ ጀምሮ፣ በአስቸኳይ የቤት ኪራይ ጣራ የሕዝብ ውሳኔ ተደርጎ፣ አድሱ የሕዝብ ምክር ቤት የመጀመርያ ሥራውን ከዛ መጀመር አለበት።
4) የኢትዮጵያ ክራይ ቤቶች በሙሉ በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት፣ በሁሉም ከተማ የቤት ኪራይ ጣራ፣ ከአንድ ኢትዮጵያዊ ገቢ ከአሥር በመቶ፣ እንዳይበልጥ ተደርጎ የውሳኔ ዐዋጅ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምክር ቤት ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ በዐዋጅ መግለጽ አለበት።
5) የኢትዮጵያ ሆቴሎች የአልጋ፣ የአንድ ሌሊት ዋጋ፣ ባለ አምስት ኰከብ ከ 150 ብር የመጨረሻ ጣራ ከ 200 ብር (ሁለት መቶ የኢትዮጵያ ብር) በፍጹም መብለጥ የለበትም። ሆቴሎች አልጋቸውን በኢትዮጵያ ውስጥ በውጭ አገር ገንዘብ ማከራየት በፍጹም የተከለከለ ነው።
6) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው፡፡
7) ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው፡፡
8) መንግሥት የጤና! የትምህርትና ሌሎች የማኅበራዊ አገልግሎቶችና የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ያከናውናል።
9) መንግሥት የአካል እና የአዕምሮ ጉዳተኞችን! አረጋውያንንና ያለወላጅ ወይም ያለ አሳዳጊ የቀሩ ሕጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡
10) መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊስና ፕሮግራሞች ያወጣል።
11) መንግሥት የባሕል እንዲሁም የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብ በተጨማሪ ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

<u>አንቀጽ አርባ ሁለት</u>

<u>የሠራተኞች መብት</u>

1) የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሰራተኞች፣ከተወሰነ ኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው፡፡ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት! ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካቲታል፡፡
2) የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፡፡

3) እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ፡፡
4) ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የዕረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደረስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው፡፡እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጐች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋል፡፡

<u>አንቀጽ አርባ ሦስት</u>

<u>የልማት መብት</u>

1) የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይም ሆነ በተናጠል የኑሮ ሁኔታውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው በሕግ ኢትዮጵያ የተጠበቀ ነው፡፡
2) ዜጐች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
3) መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገባቸው ስምምነቶችም ሆኑ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች የኢትዮጵያን የማያቋርጥ እድገት መብት የሚያስከብሩ መሆን አለባቸው፡፡ የልማት እንቅስቀሴ ዋና ዓላማ የዜጐችን እድገትና መሰረታዊ ፍላጐቶች ማሟላት ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ አርባ አራት</u>

<u>የአካባቢ ደህንነት መብት</u>

1) ሁሉም ሰዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው፡፡
2) መንግሥት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
3) የነዋሪውን ሕዝብ፣የፋብሪካና የምርት ሰራተኛውንና በአጠቃላይ አከባቢውን ለውድመትና ለጉዳት በሚዳርጉ የሥራ ዘርፎችና ተቋማት ላይ ያተኮረ መመሪያና ለነዚህን ጎጂ ውጤቶች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉትን እንቅስቃሴዎችና ተቋማት በሕግ መከልከል ይኖርበታል።ለጊዜያዊ ጥቅም ሲባል

የአሁኑንና የወደፊቱን ትውልድና አካባቢ ደህንነት ለአደጋ ማጋለጥ ትክክል አይደለም። ስለሆነም አሁን በአገራችን የተከሰተው በኬሚካል የተበከለን ከባቢ፣ወንዝና ጅረት ማጽዳት ያስፈልጋል።

4) የአካባቢና የወንዞች ወይንም የደኖች አያያዝን በተመለከተ ሃላፊነት የሚሰማው ዜጋን ለመፍጠር በአካባቢው አስተዳደርና በፌደራል አስተዳደር ህግና ደንብ መሠረት ጥብቅ አስተዳደርና ቁጥጥር ይካኼዳል።

ምዕራፍ አምስት

የማህበረሰብ መብቶች

<u>አንቀጽ አርባ አምስት</u>

1) ኢትዮጵያ እያንዳንዱ ዜጋ እንዲሁም ሁሉም ዜጋ በሕግ ፊት በእኩልነት የእኮኖሚ!
2) ማህበራዊ መብት በማጎናጽ የምታስዳደር ሀገር ናት፡፡ ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት ዕረፍት! የመዝናኛ ጊዜ! በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የዕረፍት ቀኖች! ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደረስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡
3) እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጐች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ (1) መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ፡፡

<u>አንቀጽ አርባ ስድስት</u>

14ቱ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች በቅርበት ሁሉም እኩልና በቂ የመንግስት አገልግሎትና ድጋፍ እንዲያገኙ የአስተዳደር ወሰን መሰረት የተቀመጡ ናቸው።

# <u>አንቀጽ አርባ ሳባት</u>

**14ቱ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች እና ዋና ከተሞቻቸው የስም ዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል።**

1) አርሲ ክፍለ ሀገር ..................................................አሰላ

2) ባሌ ክፍለ ሀገር........................................ጐባ

3) ጋሞጎፋ ክፍለ ሀገር ....................................አርባ ምንጭ

4) በጌምድር ክፍለ ሀገር ..................................ጎንደር

5) ጎጃም ክፍለ ሀገር .....................................ባህር ዳር

6) ሐረርጌ ክፍለ ሀገር .................................. ሐረር

7) ኢሉባቦር ክፍለ ሀገር .................................. መቱ

8) ከፋ ክፍለ ሀገር ..................................... ጂማ

9) ሸዋ ክፍለ ሀገር ..................................... አዲስ አበባ

10) ሲዳሞ ክፍለ ሀገር ............................. ሐዋሳ

11) ትግራይ ክፍለ ሀገር ........................ መቀሌ

12) ወለጋ ክፍለ ሀገር ............................ ነቀምት

13) ወሎ ክፍለ ሀገር ......................................ደሴ ናቸው ። እንዲሁም


14 የአዲስ አበባ አስተዳደር /ክፍለ ሀገር...........................................አዲስ አበባ

አዲስ አባባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ናት፡፡

15 የአፋር አስተዳደር /ክፍለ ሀገር............... ...........................አሰብ

16 የጋምበላ አስተዳደር /ክፍለ ሀገር…………………………… …  ጋምበላ

17 የኦጋደን ሶማሌ አስተዳደር /ክፍለ ሀገር …………………………… ጂጂጋ ናቸው፡፡




1) አስተዳደር ከክፍላተ ሀገር ጋር እኩል ሆኖ ተጠርነታቸው ለፌደራል መንግሥት ነው። ነገር ግን ስያሜዉ ወደ ክፍላተ ሀገር እንዲቀየር አሰፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሕዝብ ፈቃድ እስከሆነ ድረስ መዋቅሩም ስያሜዉ በሕጋዊ መንገድ ክፍላተ ሀገር ተብሎ ይጠራል፡፡

2) በህገ ኢትዮጵያ ማንኛዉም ቡድን ወይም ግለሰብ ታሪካዊ የሀገር! ስሞችና ከተሞች! መንደሮች! ታሪካዊ የሀገር ቅርሳ ቅርሶች መልክ መቀየር! ዲዛይን መለወጥ! ቀለም መፋቅ መንገዶች ስያሜን መሰጠት ወይም መቀየር በሕግ የተከለከለ ሲሆን መንገዶች ደግሞ ለሀገርና ለሕዝብን ነጻነት

የተዋደቁ ጀግኖች ስያሜ በብሄራዊ ደረጃ በሕዝብ ሲታመን ይቀየራል፡፡ ዝርዝር ወደ ፊት በሕግ ይወሰናል፡፡




ታሪካዊ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር መልክዓ ምድራዊ የአስተዳደር ካርታ

## አንቀጽ አርባ ስምንት

**14ቱ ክፍላተ ሀገሮች እኩል በሆነ በሕዝባቸው ብዛት የአገሪቱን ድርሻ ተካፋዮች ናቸው።**

## አንቀጽ አርባ ዘጠኝ

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ

፩) የ14ቱ ክፍላተ ሀገሮች ዋና ከተማቸው አዲስ አበባ ትሆናለች።

፪) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ተጠርነቱ ለፌዴራል መንግስት ሆኖ ራሱ በራሱ

የማስተዳደር ስልጣን አለው።

# ምዕራፍ ስድስት

አንቀጽ ሃምሳ

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የሕዝብ ምክር ቤት

1) የኢትዮጵያ የሕዝብ ምክር ቤት የፌደራል መንግስት ከፕሬዝዳንት በላይ ከፍተኛ ስልጣን ያለው አካል ነው! ምክንያቱም የእነሱ ኃላፊነት በቀጥታ ለወከላቸው ሕዝብ ነውና።
2) በሕገ-ኢትዮጵያ መሰረት ሁሉም የሕዝብ ተወካዮች በሕዝቡ ለአራት (4) ዓመት በአጠቃላይ አገራዊ ምርጫ ይመረጣሉ።እነሱም ከከፌዴራል ወይም ከዴሞክራትክ ፓርቲ ወይም ሪፓብልክ ፓርቲ (ሪፓ) የተወጣጡ ብቻ ናቸው።
3) እየአንዳንዱ ክፍለ ሀገር ሦስት (3) ሴነተሮች እና እየአንዳንዱ አውራጃ 1 ተወካይ መርጦ ወደ አዲስ አበባ ለአራት (4) ዓመት መላክ አለባቸው።14ቱም ክፍለ ሀገር 3 ሴነተሮችን እና አንድ ከየአውራጃዎች የተመረጡ ተውካዮችን መርጠው ለአራት (4) ዓመት መላክ አለባቸው።እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ እራሱን የቻለ 3 ሴነተሮችን መርጦ መላክ አለበት።

የሥልጣን አወቃቀር እና ክፍፍል

## አንቀጽ ሃምሣ አንድ

ስለ ሥልጣን አካላት አወቃቀር እና የሕዝብ ምክር ቤት

አባላት

ኢትዮጵያ፣ በፌዴራልና በክፍላተ ሀገር አስተዳደር መዋቅር ትዋቀራለች።

## አንቀጽ ሃምሳ ሁለት

የሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1) የክፍለ ሀገራት ምክርቤቱ በሕገ-ኢትዮጵያ ሥር ሕግን የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡በሕዝብ በሚነሱ ጥያቄዎች መሰረት ይወሰናል፡፡ሕገ ኢትዮጵያ በሕዝብ እኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ያደርጋል፡፡
2) ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጣምራ የተሰጡትን ሥልጣኖች ያከናውናል፡፡
3) በክፍለ ሀገሮች ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ይፈልጋል፡፡
4) የክፍለ ሀገራትና የፌዴራሉ መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ መንግሥት ለክፍለ ሀገሮች ድጐማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል፡፡
5) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ይለያያል፡፡ ማንኛውም ክፍለ ሀገር ይህን የሕገ-ኢትዮድያን ሥርዓት በመጣስ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፡፡

### አንቀጽ ሃምሣ ሦስት

የሕዝብ ምክር ቤት አባላት መብት

1) የኢትዮድያ ሕዝብ በሪፈረንደም የሕግ የበላይነት ሕገ ኢትዮድያን ካፀደቀ ቀን ጀምሮ አሁን ያለው ፓርላማ ሙሉ በሙሉ ይከስማል።

2) የኢትዮጵያ ሕዝብ በሪፈረንደም የሕግ የበላይነት ሕገ ኢትዮጵያን ካፀደቀ ቀን ጀምሮ አሁን ያለው የፓርላሜንት ሥርዓት የኢትዮጵያ ኮንግረስ ወይም የሕዝብ ምክር ቤት ተብሎ ይጠራል።
3) የኢትዮጵያ ኮንግረስ ወይም የሕዝብ ምክር ቤት የሚባለው፣ የሴናተሮች ወለልና የሕዝብ ተወካዮች ወለል አንድ ላይ ሆነው የበታች ሕግ ወይም የአገሪቱን ሕገ መንግሥት በየግዜው የሚያወጣና የሚወስን የሕዝብ ምክርቤት ጉባኤ ተብሎ ይጠራል።
4) ማንኛውም የሕዝብ ምክር ቤት አባል በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በሚሰጠው አስተያየት ወይም ድምጽ ምክንያት ያለመከሠስ መብቱ ይጠበቅለታል፤ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡
5) ማንኛውም የሕዝብ ምክር ቤት አባል ወንጀል ሲፈጽም ከተገኘ ፣ በአንቀፅ 4 በቁጥር 2 ላይ በተደነገገው መሠረት ፕረዝዳንቱን ጨምሮ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በፍርድ ፊት ዕኩል ነው በሚለው መርህ መሠረት ሁሉም በወንጀል ዕኩል መከሰስ አለበት።

<u>አንቀጽ ሃምሣ አራት</u>

ውሳኔዎችና የሥነሥርዓት ደንቦች

1) የሕዝብ ምክር ቤት ተወካዮች በፌዴራልም ሆነ በክፍለ ሀገራት ለ4 ዓመታት ሥራ አገልግሎት በቀጥታ በሕዝብ የተመረጡ ብቻ ናቸው።
2) የሕዝብ ምክር ቤት ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡ ማናቸውም ውሳኔ የሚያልፈው በስብሰባ ላይ ከተገኙት የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ድምጽ ሲደገፍ ብቻ ነው፡፡
3) አባላት ድምጽ መስጠት የሚችሉት በአካል ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

<u>አንቀጽ ሃምሳ አምስት</u>

ስለበጀት

የሕዝብ ምክር ቤት ቅዲሚያ የኢትዮጵያ ትንሳዔ የእርሻ አጠቃቀም ፕላን ለ14ቱም ክፍለ ሀገራት ገበሬውን በማህበር በማደራጀት ለ14ቱም ክፍለ ሀገር ገበሬ ማህበር እኩል በሆነ መልክ ፤

1) ዘመናዊ የእርሻ መሣርያ ትራክተር
2) ኮምባይነር

3) ሰው ሠራሽ የዝናብ መሣሪያ የማስገባት እያንዳንዱ አርሶ አደር የኢኮኖሚ መሻሻል የኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ የፌዴራል መንግሥት ሥልጣንና አርሶ አደሩ ለፈጣን እኮኖሚ እድገት ተጠቃምነት በጋራ የመሥራት እና የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የኢትዮጵያ ሕዝብ እድገት የእርሻ አግሮካልቸር እንዳስተሪ መሪህ የመነሻ መሠረት ፖለስ ይከተላል፡፡
4) የሕዝብ ምክር ቤት የእርሻ አግሮካልቸር በጀቱን ቀምር ያዘጋጃል፡፡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠቅላላ ጉብኤ በማቅረብ ያስወስናል፡፡

አንቀጽ ሃምሣ ስድስት

የምክር ቤቱ አፈጉባኤ ሥልጣን

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አፈጉባኤ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡
2. ምክርቤቱን በመወከል ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል፡፡
3. ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ የወሰነውን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፡፡

<u>አንቀጽ ሃምሳ ሳባት</u>

<u>ስብሰባና የሥራ ዘመን</u>

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የሥራ ዘመን 4 ዓመት ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ ሃምሳ ስምንት</u>

በሁለቱም ምክር ቤቶች አባል መሆን የማይቻል ስለመሆኑ

1) ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ሊሆን አይችልም፡፡

<u>አንቀጽ ሃምሳ ዘጠኝ</u>

<u>ስለ ሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት</u>

1) ፕሬዚዳንቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሪ ነው፡፡

2) የኢትዮድያ ሕዝብ የሕግ የበላይነት ሕገ ኢትዮድያን በሪፈሬንደም ካፀደቀ ቀን ጀምሮ የጠቅላይ ሚንስቴር ሥርዓት ወደ ፕሬዝዳንት ሥርዓት ይቀየራል።

3) አሁን ያለው ጠቅላይ ሚኒስቴር እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ ጊዜያዊ ፕረዝዳንት ሆነው ያገለግላሉ። ለሚቀጥለው ብሄራዊ ምርጫ ውስጥ ለፕሬዝዳንትነት ለመፎካከር ከፈለገም፣ ከሦስቱ ፓርቲዎች በፌዴራል፣ በዴሞክራትክ እና፣ በሪፓብልክ ውስጥ ተመዝግበው ለመፎካከር መብት አለው።

## <u>አንቀጽ ሥልሳ</u>

<u>የኘሬዚዳንቱ አሰያየም</u>

1) የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት በመስፈርቱ መሠረት በኢትዮጵያ ሕዝብ በ14ቱም ክፍለ ሀገራት ተወዳድሮ አንድ ሰው አንድ ድምፅ መሠረት (one person one vote rule) ያሸነፈ ወይም ያሸነፈች ሰው ይሆናል።

2) የኘሬዚዳንቱ የሥራ ዘመን አራት (4) ዓመት ይሆናል፡፡ አንድ ሰው ከሁለትጊዜ በላይ ለኘሬዚዳንትነት ሊመረጥ አይችልም።

3) የሪፐብሊኩ ኘሬዚዳንት ምርጫ ከጸደቀ በኃላ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የጋራ ስብሰባው በሚወስነው ጊዜ በስብሰባው ፊት ለሕገ-ኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ታማኝነት በሚተከለዉ ከታቻች በተገለጸ መሠረት ቃለ በመሃላ ይፈጸምል፡፡
«እኔ.......በዛሬው ዕለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኘሬዚዳንት በመሆን ሥራዬን ሲጀምር ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብና እናት ሀገር ለማገልገል የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነት እና በቅን ልቦና በቅንነት መንፈስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማገልገል ቃል እገባለሁ፡፡»

<u>አንቀጽ ስድሣ አንድ</u>

<u>የኘሬዚዳንቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የሰናተሮች ዓመታዊ የጋራ ስብሰበባ ይከፍታል፡፡

2. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቃቸው ሕጐችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በነጋሪትጋዜጣ ያውጃል፡፡

3. ሀገሪቷን በውጭ ሀገሮች የሚወክሉትን አምባሳደሮችና ሌሎች መልክተኞች ይሾማል፡፡

4. የውጭ ሀገር አምሳደሮችንና የልዩ መልዕክተኞችን የሹመት ደብዳቤ ይቀበላል፡፡

5. በሕግ መሰረት ኒሻኖችና ሽልማቶችን ይሰጣል፡፡በተጨማርም በሕግ በተወሰነው መሰረት ከፍተኛ የውትድርና ማዕረጐችን ይሰጣል፡፡

6. የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ሊቀመንበር ነው ወይም ናት። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት አባላት የፕሬዝዳንት ካብነዎች፣ እና ከፍተኛ የደህነት አማካሪዎችን ያጠቃልላል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና በውጭ ፖሊሲ ላይ በመመካከር የተላለፉ ጉዳዮችን ለመጨረሻ ውሳኔ ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ምክር ቤት በማቅረብ እንዲፀድቁለት ይጠይቃል።

## አንቀጽ ስድሳ ሁለት

### የሕግ አስፈጻሚ አካል

### ስለ አስፈጻሚነት ሥልጣን

1) የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ከማዕከላዊ መንግስት ጋር ዕኩል ሥልጣን ያለው ነው፡፡

## አንቀጽ ስድሣ ሦስት

### የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

1) የሀገሪቱ ርዕሰ መስተዳድር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ነው፡፡
2) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎችን ከሁለቱ ምክር ቤቶች አባላት ወይም ለሥራው ብቃት ካላቸው ሌሎች ግለሰቦች መካከል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በእጩነት አቅርቦ ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡
3) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚያወጣቸውን ሕጐች፣ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡
4) የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይመራል! ያስተባብራል፣ ይወክላል፡፡
5) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ደንቦች መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነት ይከተተላል፡፡

6) የሀገሪቱን የውጭ ፖሊሲ በበላይነት ያስፈጽማል፡፡

7) ኮሚሽነሮችን፣በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡

8) የመስተዳድሩን ሥራ አፈጻጸምና ብቃት ይቆጣጠራል! አስፈላጊ የሆኑ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

9) ከፍተኛ የመንግሥት ሲቪል ሹመቶችን ይሰጣል፡፡

10) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ወይም በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ኒሻኖችንና ሽልማቶችን ይሰጣል፡፡

11) ስለ ሀገሪቱ ሁኔታ ፣በመንግሥት ስለ ተከናወኑ ተግባራትና ስለ ወደ ፊት እቅዶች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖረት ያቀርባል፡፡

12) በመንግሥትና በሌሎች ሕጐች የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡

13) ሕገ ኢትዮጵያን ያከብራል! ያስከበራል፡፡

<u>አንቀጽ ስድሳ አራት</u>

<u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት</u>

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንቱ በሕግ በሚወሰን መሰረት ሌሎች አባሎች የሚገኙበት ምክር ቤት ነው፡፡
2) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ነው፡፡
3) የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወስነው ውሳኔ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ መፅደቅ አለበት።

<u>አንቀጽ ስድሳ አምስት</u>

<u>የፌዴራሉን መንግሥት ዓመታዊ በጀት</u>

1. የፌዴራሉን መንግሥት ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል ፣ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፡፡ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ይበደራል፣ የአገሪቱ ገንዘብ ማሳተም፣ የውጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልውውጥን ይቆጣጠራል፡

<u>አንቀጽ ስድሳ ስድስት</u>

<u>የውጭ ግንኙነት መርሆዎች</u>

1) የፌደራል መንግስት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማራመድ፡፡
2) የፌደራል መንግስት የመንግሥታትን ሉዓላዊነትና እኩልነት ማክበር፣ በሌሎች ሀገሮች ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፡፡
3) የፌደራል መንግስት የሀገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እንዲሁም በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ስምምነቶች የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
4) የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩና የሕዝቧን ጥቅም የማይጻረሩ ዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶችን ማክበር፡፡
5) ከጐረቤት ሀገሮችና ከሌሎችም የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ኅብረትና የሕዝቦች ወንድማማችነትን ማጐልበት፡፡
6) በሀገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ

# <u>አንቀጽ ስድሣ ሳባት</u>

የመከላከያ መርሆዎች

1. በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት የኢትዮጵያ ፕረዚዳንት ሥልጣንና የመከላከያ ሰራዊት አገልግሎት መለያየት አለበት።ያ ማለት የኢትዮጵያ ፕረዚዳንት እንደተለመደው የጠቅላይ ጦር አዛዥ ለመሆን አይችልም ማለት ነው።

2. በሕገ ኢትዮድያ መሠረት የኢትዮድያ መከላከያ ሚኒስቴር ስቪል ነው። የሚሾመውም በኢትዮድያ ሕዝብ ምክር ቤት በአብላጫ ድምፅ ነው። የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ሚኒስቴር ወንድ ወይም ሴት መሆን ይችላል።

3. የኢትዮድያ ሕዝብ ብሔራዊ የሕግ የበላይነት ሪፈሬንደም ካፀደቀ ቀን ጀምሮ የኢትዮድያ መከላከያ ሚኒስቴርና፣ የሕዝብ ደህንነት ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከፐሬዝዳንት ሥልጣን ሥር፣ ሙሉ በሙሉ ተለይተው ነጻና ገለልተኛ ተቋም ይሆናሉ። ምክንያቱም ይህ ተቋም በአገራችን ውስጥ የህግ

የበላይነት ክብርና የህዝባችንን ደህንነት የሚያስጠብቅ እጅግ ተከብሮ ለዘለዓለም የምቀጥል ይሆናል እንጂ፣ መንግሥት በተቀየረ ቁጥር፣ ያ ታላቁ ውሌታቸው በሜዳ ላይ ተጥሎ በየመንገድ ላይ ተበትነው የምለምኑ አይሆኑም፤ ይልቁንስ፣ ከእንግድህ ወዲህ የነሱ ታላቁ ውሌታ፣ ለአገራችን ወደርየለሽ የከፈሉበት ዋጋ፣ ለእኛና ለሚመጣው ትውልድ በክብራቸው ላይ ክብር እየተጨመረላቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገራል።

4. የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ሚኒስቴር እጩዎችን የሚያቀርበው የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት  በድምፅ ብልጫ መርጦ ሲሆን፣ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኢትዮድያ ሕዝብ ምክር ቤት በማቅረብ እንድያልፍ ካደረገ በኃላ በኢትዮድያ ፕሬዝዳንት ፊርማ ይፀድቃል።

# አንቀጽ 68

# የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት

1) የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት በሕዝብ ድምፅ ቢልጫ የተመረጡ ሰባት አባላት ይኖሩታል። የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት አባላት የአገልግሎታቸው ዘመን አራት ዓመት ብቻ ይሆናል። ነገር ግን በየአራት ዓመት እንደገና ለመፎካከር ምንም የጊዜ ገደብ የለባቸውም።

2) የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት አባላት ከማናቸውም ፖሌትካ ፓርትዎች ወይም በአንቀጽ 39 ላይ የተደነገጉ ፌደራል፣ ደሞክራትክ፣ ሪፓብልክ፣ ፓርትዎች አባልነት ነፃ የሆኑ መሆን አለባቸው።

3) የኢትዮድያ ፕሬዝዳንት የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት ሊቀመንበር ይሆናል።

4) የኢትዮድያ ፕሬዝዳንት የኢትዮድያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት በሚመለከት ጉዳይ ላይ፣ ያለ ምክር ቤቱ ድምፅ ብልጫ ውሳኔ በስተቀር፣ የኢትዮድያ ፕሬዝዳንት ምንም ዓይነት ውሳኔ ለማድረግ አይችልም። ነገር ግን የኢትዮድያ ፕሬዝዳንት ይህንን ሕግ ጥሶ ቢገኝ ምክር ቤቱ ለኢትዮድያ ሕዝብ ምክር ቤት አቅርቦ ፕሬዝዳንቱን መቅጣት፣ ወይም ከሥልጣናቸው እንድሰናበት ማስደረግ ይችላል።

5) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ዕጩዎችን በድምፅ ብልጫ መርጦ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምክር ቤት አቀርቦ በድምፅ ብልጫ ይፀድቃል። ከዚያም፣ የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ይፈርማል።

6) የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት የሀገሪቱን ጠቅላይ ጦር አዛዥ ከሥልጣናቸው ለማሰናበት ምንም ዓይነት ሥልጣን የለውም። የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥን ከሥልጣናቸው ማሰናበት የሚችለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምክር ቤት በማቅረብ ካፀደቀ ብቻ ነው።

7) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ በሚመለከት፣ በግንባር ቀደምትነት ማናቸውንም ጉዳይ ለመፈፀም ሙሉ ኃላፊነት አለበት።

8) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ በሚመለከት ለሚያደርሰው ጥፋት፣ በግንባር ቀደምትነት ማናቸውንም ጉዳይ ለመቆጣጠር፣ የጠበቀ ክት ትል ለማድረግ፣ ሙሉ ሥልጣን አለው።

9) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት፣ የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ በሚመለከት፣ በግንባር ቀደምትነት ማናቸውንም ጉዳይ ለመቆጣጠር፣ በሕግ የበላይነት መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉም ዕኩል የደህንነት ጥበቃ በትክክል በተግባር ማግኘቱን፣ በተለይ የሕዝብ እርስ በርስ ጥላቻና ጥል ያለመኖሩን በጥብቅ ይከታተላል።

10) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት፣ የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ በሚመለከት፣ በግንባር ቀደምትነት ማናቸውንም ጉዳይ፣ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ሁሉም ዕኩል የደህንነት ጥበቃ በትክክል በተግባር ማግኘቱን፣ በተለይ የደን እሳትን በሚመለከት ሁሉም ክፍላተ ሀገር በቂ መሣሪያ አየርን ጨምሮ የተሟላ መኖሩን በጥብቅ ይከታተላል።

11) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት፣ የሀገሪቱን ብሔራዊ ማንኛውንም <u>ድንገተኛ አደጋ መከላከያ</u> በሚመለከት፣ በግንባር ቀደምትነት ማናቸውንም ጉዳይ፣ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ሁሉም ዕኩል ጥበቃ በትክክል በተግባር ማግኘቱንና፣ በተለይ በቂ መከላከያና <u>ማምለጫ መሣሪያ አየርን</u> ጨምሮ የተሟላ መኖሩን በጥብቅ ይከታተላል።

## አንቀጽ 69

## የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ

1) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ የሚሾመው በኢትዮጵያ ሕዝብ ምክር ቤት ቀርበው አብላጫ ድምፅ ያገኘ ሲሆን፣ ተፎካካሪዎች አንድ ዕጩ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ሲሆን፣ ሌሎች ኢትዮጵያውያን በግላቸው በዕውቀታቸው፣ በችሎታቸው፣ በተስጦታቸው፣ ቀርበው በመመዝገብ ለሥራው መፎካከር ይችላሉ።
2) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ማንኛውንም የኢትዮጵያ ጦር ኃይል የመምራትና የኢትዮጵያን ጦር መሣሪያና የሰው ብቃት፣ የጦር መሣሪያ ምንጭ የማፍለቅ ኃላፊነት አለበት።
3) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ማንኛውንም የጦር እስትራተጂና ዕቅድ፣ የመሣሪያ ምንጭ ለማግኘት ሁሉ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ምክር ቤት ሪፖርት ማድረግ አለበት።
4) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ማንኛውንም የጦር እስትራተጂና ዕቅድ፣ የመሣሪያ ምንጭ ለመገንባት፣ የሀገሪቱን የጦር ሎጂስትክ ለሟሟላት በቂ ችሎታና ልምድ ያለው መሆን አለበት።
5) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ማንኛውንም የጦር እስትራተጂና ዕቅድ፣ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የጦር ኃይል ሠራዊት ለመገንባት፣ በቂ የጦር ሎጂስትክ ለመገንባት፣ የምድር፣ የባሕር ኃይል፣ የአየር ኃይል ለመገንባት፣ በቂ የሰው ኃየል ለማሠልጠን በቂ ችሎታና ልምድ፣ የስትራተጂ ዕውቀት ያለው መሆን አለበት።
6) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ፣ በቂ የሰው ኃየል በመካናይዝድ ብርጌድና፣ ዘላቂ የሎጂስትክ አቅርቦት ለማቅረብና ለማሠልጠን፣ ያለውንም ለማሻሻል በቂ ችሎታና ልምድ ያለው መሆን አለበት።
7) ተፎካካሪዎች ሲቭል ሆነው 100 ፐርሰንት በአባትም በእናትም ኢትዮጵያዊ ሆነው በአገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ነዋሪ የሆኑ ሁሉ የመፎካከር መብት አላቸው።
8) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ፣ የአገልግሎት ዘመን ለአአራት ዓመት ብቻ ነው። ነገር ግን በየ 4 ዓመት እንደገና ለመወዳደር ይችላል። የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ዋና የሥራው ተግባር የአገሪቱ የውስጥና የውጭ ደህንነት ከመከላከያ ጀነራሎች ከሚቀርበው ሀሳብና ምክር ውሳኔ መሠረት ተግባራዊ ማድረግ ነው።
9) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የደህንነት ምክር ቤት፣የኢትዮጵያ የመከላከያ ጀኔራሎች፣ በአንድነት በመመካከር ኢትዮጵያን ወደ ዘመናዊ ጦር መሣርያ ዕድገት ወይም ወደ ኤሌክትሮኒክ ሪቮሉሽን ለማሻገር የሰው ኃይል በአገር ውስጥና ወጣቶችን ወደ የተለያዩ ሀገሮች ልኮ ለማሰልጠን የኢትዮጵያ የሕዝብ ምክር ቤት በቂ በጀት እንዲመደብላቸው መጠየቅ አለበት።

# አንቀጽ 70

# የኢትዮጵያ ብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት

5. የኢትዮድያ ዜጋ የሆነ ሁሉ፣የ12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች፣የአካል ብቃት ያላቸው፣ ዕድሜአቸው ከ18-32 ድረስ ያሉ ወጣቶች ከ6 ሺ ብር መነሻ አድርጎ የኢትዮጵያ የሕዝብ ምክር ቤት በሚወስነው ክፍያ መሠረት ለ2 ዓመት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት መፈጸም አለባቸው።ነገር ግን ወጣቶቹ ለጥቅማቸው ሲሉ በፍቃዳቸው እንጂ መንግስት ለብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት በግዳጅ ማንንም መላክ እንደማይችል ሕገ ኢትዮድያ መንግስትን ይገድባል። ማንኛውም የኢትዮድያ ወጣት የሁለት ዓመት ብሔራዊ ውትድርና ግዳጁን ከፈፀመ በኃላ፣ ሙሉ ነፃ የትምህርት ዕድልና፣ የጤና እንሹራስ እንክብካቤ ማግኘት አለበት።

6. የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት ከአድስ አበባ ጋር ከ14ቱ ክፍላተ ሀገር ዕኩል በሆነ መልክ የተወጣጣ መሆን አለበት። እንድሁም መከላከያና የደህንነት ሚኒስቴር፣ ከማናቸውም ፖለትካ ፓርትዎች ነፃና ገለልተኛ ተቋም ነው።

7. በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት የኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስተር ሆኖ የሚሾመው በሴናተሮችና በሕዝብ ተጠሪዎች ወለል አንድ ላይ (የሕዝብ ምክር ቤት) ከፍተኛ ውይይት ተደርጎ የተመረጠ ሲቪል መሆን አለበት።

8. የመከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡

9. የመከላከያ ሠራዊቱ በማናቸውም ጊዜ ለሕገ-ኢትዮጵያ ተገዢ ይሆናል፡፡

10. የመከላከያ ሠራዊቱ ተግባሩን ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊነት ነጻ በሆነ አኳኃን ያከናውናል፡፡እንዲሁም፣ የአገራችን ፌደራል ጦር አዲስ አበባን ጨምሮ ከየክፍለ ሀገር ዕኩል የተወጣጣ እንጂ በሕዝብ ብዛት እየተባለ የአንድ ጎሳ፣ ወገን አብላጫ ማድረግ ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

11. በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት በሕገወጥ መንገድ መሣርያ መታጠቅ የተከለከለ ነው።ነገር ግን የፀጥታ ሥጋት ያለባቸው አከባቢ ራሳቸውን ከአሸባሪዎች ለመጠበቅ በሕጋዊ ፈቃድ ለመጠቀም እንዲችሉ

የየአከባቢ የሕዝብ ምክር ቤት መወሰን አለበት።ከዚያ ውጭ ሕገወጥ መሳሪያ ይዞ መገኘት በገንዘብና በእስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው። ዝርዝሩ በሕዝብ ምክር ቤት በሕግ ይወሰናል።

12.በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት አንድ ወገን ተነስቶ ወረራ በማድረግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በብሔራቸው በጎሳቸው ምክንያት ለይቶ ከኖሩበት ሥፍራ እንዲለቁ ተብለው ወንድ ወይም ሴት፣ ሕጻናት ወይም ሽማግሌዎችን፣ አሮጊቶችና አካሌ ስንኩላንን በግፍ የገደሉ ሁሉ፤ ሰዎችን ከቤት ንብረታቸው ማፈናቀል፣ የእምነት ተቋሞችን ማቃጠል የንፁህን ደም ማፍሰስ እና ሰው መግደል ወንጀለኞቹ በፍርድ ቤት የተረጋገጠባቸው ግለሰቦች በሙሉ፤ በአደባባይ የሞት ቅጣት መቀበል አለባቸው። የዚህ ዓይነት ወንጀል ክስ ምንግዜም በይርጋ አይታገድም።

13. በዚህ በኢ . ፌ. ዲ. . ሪ . ግፈኛ ሥርዓት ውስጥ ቤተሰብ የተገደለባቸው ሁሉ ባል ወይም ሚስት በሕይወት የተረፉት ከመንግስት 10 ሚልዮን የኢትዮድያ ብር ካሣ ልከፈላቸው ይግባል።

14. አባት ወይም እናት የተገደሉባቸው ልጆች፣ የአባታቸውን ወይም የእናታቸውን የደም ካሣ ከመንግሥት እያንዳንዳቸው 10 ሚልዮን የኢትዮድያ ብር ካሣ ልከፈላቸው ይግባል። በዚህ ዓይነት አካል ስንኩላን የሆኑትን ሁሉ ይጨምራል።

<u>አንቀጽ 71</u>

<u>ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች</u>

1. መንግሥት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመሥረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡
2. የፌዴራል መንግሥት ተወካዮች በቁጥር በተወሰኑ ጉዳዮች በሚመለከት ከክፍለ ሀገር አስተዳደር ጋር በስምምነት ልሰሩ ይችላሉ! ነገር ግን የፌዴራል መንግሥት ተወካዮች ያለክፍለ ሀገሩ ፈቃድ የፌዴራል መንግሥት በክፍለ ሀገር ጉዳይ ውስጥ እንዳይገባ ሕገ ኢትዮጵያ በጥብቅ ይከለከላል።
3. እንዲሁም መንግሥት የሕዝብን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነት አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፡፡
4. ኢትዮድያ ለረጅም ዘመናት ዜጎቿን ያለአንዳች ልዩነት በየክፍለ ሀገራቸው አብረው ተከባብረው እንድኖር ያደረገች አገር! አሁንም ለወደፊት የምታደርግ አገር ናት።

5. የየክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪዎች የፌደራል መንግስት ስልጣን በየክፍለ ሀገር አስተዳደር ላይ በጣም ውስን መሆኑን ማወቅ አለባቸው።

6. እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የየክፍለ ሀገሩ ክብር ጠብቆ ራሱን በራሱ እያስተዳደረ መቀጠል አለበት።

ምዕራፍ ሰባት

<u>አንቀጽ 72</u>

<u>ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች</u>

1. በሕገ ኢትዮጵያ የፌደራል መንግስትንና የክፍላተ ሀገር መንግስት አንድ ላይ ተቀራርበው ለአንድ አገር መሥራት አለባቸው።መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት፡፡

2. የፌደራል መንግስት በክፍለ ሀገር መንግስት ጋር የሥራ ትብብር ድርሻ ለመካፈል እንጅ የፌደራል መንግስት በክፍለ ሀገር ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዲገባ ሕገ ኢትዮጵያ አይፈቅድም።መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡የክፍለ ሀገር መሪዎች ግንኙነት ማጠናከር አለበት። የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጐጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲ ደርስ ማድረግ፡፡በእድገት ወደኃላ ለቀሩ ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3. የፌደራል መንግስት በክፍላተ ሀገር ጉዳይ ላይ በስምምነት ለመረዳዳት ካልሆነ በስተቀር፣ ፌደራል በክፍለ ሀገር አስተዳደር ውስጥ ምንም ዓይነት ጣልቃ እንዳይገባ ሕገ ኢትዮጵያ በጥብቅ ይገድባል።መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ሥም በይዞታው ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክር (የሴነትና የሕዝብ ተጠሪዎች ወለል) የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር የገብና የወጭ መዋቅር ለማውጣት አይችሉም።ነገር ግን የክፍላተ ሀገር መንግስት በነፃነት በሕገ ኢትዮጵያ ሥር የራሱን በክፍለ ሀገሩ ሕግ መሰረት የክፍለ ሀግሩን መዋቅር የማውጣት ሙሉ ሙብት አላቸው።የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግሥት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት፡፡ የሕዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፡፡

5. የኢትዮጵያ የፌደራልና የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ፍርድ ቤቶች የክፍላተ ሀገር ፍርድ ቤቶች ሕግና ደንብ በሕገ ኢትዮጵያ መሠረት መሆኑን ማጣራትና ማክበር አለባቸው። መንግሥት በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት

   አለበት፡፡

6. የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ለእድገትና ለብልፅግና ከፌደራል መንግስት ጋር ተቀናጅቶ የሚሠሩ ተግባራትን በጋራ እየሠሩ የራሳቸውን የክፍላተ ሀገር ተግባር ግን በራሳቸው በክፍለ ሀገሩ ሕግ መሠረት ብቻ የፌደራል መንግሥት ምንም ጣልቃ ሳይገባ መሥራት አለባቸው። መንግሥት የዘጎችን ጤንነት፣ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት፡፡

7. የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ማንኛውንም ከፌደራል መንግሥት የሚመጣ የገቢ ድርሻ እንደ አስፈላግነቱ መጠቀም እንጂ በአንድ ቦታ ብቻ ገድበው መጠቀም የለባቸውም።

8. የኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት በክፍላተ ሀገርና በተለያዩ በክፍለ ሀገሩ ድርጅቶች ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የማድረግ ሥልጣን የለውም።

<u>አንቀጽ 73</u>

<u>ማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች</u>

1. የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣የጤና አገልግሎት፣የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

2. ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት፣ከፖለቲካ አመለካከቶች እና ከባህላዊ ተፅእኖዎች ነጻ በሆነ መንገድ መካሔድ አለበት፡፡

<u>አንቀጽ 74</u>

<u>ባሕል ነክ ዓላማዎች</u>

1) መንግሥት መሰረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን የማይቃረኑ ባሕሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጐለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡
2) የሀገር የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው፡፡

3) መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን፣ሳይንስንና ቴኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት፡፡

አንቀጽ 75

የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት፡፡
2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት፡፡
3. የሕዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ሕዝብ ሁሉ ሐሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት፡፡
4. መንግሥትና ዜጐች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 76

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

ስለ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1) የውጭ ወረራ ሲያጋጥም ወይም ሕግ ማስከበር ሥርዓት ለመቋቋም የማይቻል ሲሆን፣ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት፣ የፌዴራሉ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመደንገግ ሥልጣን አለው፡፡
2) የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት ክፍለ ሀገራት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሊያውጁ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በመንግሥት ይወሰናል፡፡
3) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ ላይ ባለ ጊዜ የታወጀ ከሆነ በታወጀ በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ አለበት አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት ሦስተኛው ድምጽ ተቀባይነት ካላገኘ ወዲያውኑ ይሻራል፡፡
4) የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣቸው ደንቦች መሰረት የሀገርን ሰላምና ሕልውና፣ የሕዝብን ደህንነት፣ሕግና ሥርዓትን የማስከበር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

አንቀጽ 77

የፋይናንስ ወጪን በሚመለከት

1. የፌዴራሉ መንግሥትና ክፍለ ሀገራት በሕግ የተሰጧቸውን ኃላፊነቶችና ተግባሮች ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በየበኩላቸው ይሸፍናሉ፤ ሆኖም ማንኛውም በውክልና ለሚፈጽመው ተግባር የሚያስፈልገው ወጪ ሌላ ስምምነት ከሌለ በቀር ውክልናውን በሰጠው ወገን ይሸፈናል፡፡

2. የፌዴራሉ መንግሥት ለክፍለ ሀገራት የተመጣጠነ እድገት እንቅፋት ካልሆነ በስተቀር ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ መቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ብድርም ሆነ እርዳታ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት ለክፍለ ሀገራት ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጐማ በሚመለከት ኦዲትና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

<u>አንቀጽ 78</u>

<u>የፋይናንስ ገቢን በሚመለከት</u>

1) የፌዴራሉ መንግሥትና ክፍለ ሀገራት የሚዋቀረውን የፌዴራል አደረጃጀት የተከተለ የገቢ ክፍፍል ያደርጋሉ፡፡

## <u>አንቀጽ 79</u>

# የፌዴራል መንግሥት የታክስና የግብር ሥልጣን

1. የፌዴራል መንግሥት በወጪና ገቢ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቀረጥ፣ የታክስና ሌሎች ክፍያዎች ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
2. በፌዴራል መንግሥትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
3. በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሆኑ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ ይጥላል፣ይሰበስባል፡፡
4. በብሔራዊ የሎተሪ እና ሌሎች የንግድ ሥራዎች ዓመታዊ ገቢ መንግስት ላይ ታክስ ይጥላል ይሰበስባል፡፡
5. በአየር! በባቡርና በባሕር ትራንስፖርት ገቢዎች ላይ ታክስ ይጥላል! ይሰበስባል፡፡
6. በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤ ኪራይ ይወስናል፡፡

7. የፌዴራል መንግሥት አካላት ከሚሰጧቸው ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፡፡

8. የፌዴራል የቴምብር ሽያጭ ቀረጥ ይጥላል ይሰበስባል፡፡

9. ከውጭ ወደ አገር ቤት የሚገቡ ዕቃዎች የጉሙሩክ ቀረጥ ታሪፍ 5. 63 % ብቻ መሆን አለበት።

10. ማንኛውም ከውጭ ወደ አገር ቤት የሚገቡ የኤሌክትሮኒክ ዕቃ በሙሉ ከጉሙሩክ ቀረጥ ታሪፍ ነጻ ናቸው።

11. ማንኛውም ከውጭ ወደ አገር ቤት የሚገቡ ዕቃዎች ያገለገለ ዕቃ በሙሉ መኪናዎችን ጨምሮ የጉሙሩክ ቀረጥ ታሪፍ 1. 3 % ፐርሰንት ብቻ መሆን አለበት።

12. ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች የጉሙሩክ ቀረጥ ታሪፍ 13% ፐርሰንት ብቻ መሆን አለበት።

13. ማንኛውም የሚገቡም ሆነ ለሚወጡ ዕቃዎች የጉሙሩክ ቀረጥ ታሪፍ ደምበኞች የምከፍሉት፣ የኢንሹራንስና የትራንስፖርት ደረስኞች ወጪ ተደምረው ከዕቃው ዋጋ ላይ ከተቀነሱ በኃላ ብቻ ነው።

የፌዴራል መንግሥት ታክስ ታሪፍ፣

1) የፔሮል ታክስ= 3 %

2) የሽያጭ ታክስ = 3 %

3) የመሬትና የቤት ታክስ = 0. 12 %

4) ፋብሪካና የኮርፖረሽን ታክስ = 5 %

5) የቤትና የዕቃ አከራዮች ታክስ = 0 %

አንቀጽ 80

ክፍለ ሀገራት የታክስና የግብር ሥልጣን

1) ክፍለ ሀገራት በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
2) በኅብረት ሥራ ማኅበራት በተደራጁ ገበሬዎች ላይ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
3) በክፍለ ሀገራት በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡

4) በክፍለ ሀገራት ውስጥ በውኃ ላይ ከሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
5) በክፍለ ሀገራት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይስ ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
6) ክፍለ ሀገራት በማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ ክፍያዎች ይጥላሉ፣ይሰበስባሉ፡፡
7) በክፍለ ሀገራት አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎች ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
8) ክፍለ ሀገራት ከደን የሚገኝ ክፍያ ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡

## የክፍለ ሀገር ታክስ ታሪፍ፣

1) የፔሮል ታክስ= 5 %
2) የሽያጭ ታክስ = 5 %
3) የመሬትና የቤት ታክስ = 0.13%
4) ፋብሪካና የኮርፖረሽን ታክስ = 7 %
5) የቤትና የዕቃ አከራዮች ታክስ = 9.3 %

## አስተዳደር ታክስ ታሪፍ፣ (አድስ አበባ፣ ጋምበላ፣ አፋር፣ ኦጋዴን ሶማሌ)

1) የፔሮል ታክስ= 5 %
2) የሽያጭ ታክስ = 5 %
3) የመሬትና የቤት ታክስ = 0. 13%
4) ፋብሪካና የኮርፖረሽን ታክስ = 7 %
5) የቤትና የዕቃ አከራዮች ታክስ = 9.3 %

## አስተዳደር ፌዴራል ታክስ ታሪፍ፣

1) የፔሮል ታክስ= 3 %
2) የሽያጭ ታክስ = 3 %
3) የመሬትና የቤት ታክስ = 0. 12%
4) ፋብሪካና የኮርፖረሽን ታክስ = 5 %

5) የቤትና የዕቃ አከራዮች ታክስ = 0 %

# አንቀጽ 81

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ሀብት፣ የጋራ የታክስና የግብር ሥልጣን

1) የፌዴራል መንግሥትና ክፍለ ሀገራት በጋር በሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ይሰበስባሉ፡፡
2) በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና በባለ አክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
3) በከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና በማናቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብር ክፍያዎች በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
4) በፈደራል መንግስት ሥር የሚተዳደሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ሀብት ድፍድፍ ነዳጅ ፔትሮለም ወርቅ! አልማዝ ዳይመድ ቴንታለም! ፖታሽየም ትላልቅ ወንዞች! ግድቦች አየር መንገድ! መርከቦች ወደብ! ቴሌኮሚኒከሽን! ብሄራዊ ሎቴሪ አስተዳደር ቴልሽዠን ጣብያ! የሬድዮ ማእከል በመንግስት ሥር ያሉ ይዞታዎች ማእድኖች! የባቡር መንገዶች፣ ባንኮችና እንሹራሶች፣ ብሄራዊ ፓርኮች የሚገኘዉ ገቢ ታሪካዊ ብሔራዊ ሀብቶች ሕልተን ሆተል፣ ግዮን ሆተል፣ የቱርስት ድርጅቶችና ገቢዎች፣ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል፣ የአድስ አበባ ዩኒቬርስቲ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት ሆኖ ለሀገርቱ ሕዝብ በእኩልነት ለመሠረተ ልማት ጥቅም ይሰጣል፡፡
5) በዚህ አንቀፅ 78 በቁጥር 4 ላይ፣ ለምሳሌ የተዘረዘሩትና ያልተዘረዘሩት ማንኛውም የተፈጥሮ ሀብት፣ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ሀብት ስለሆኑ በፈደራል መንግሥት ሥር መተዳደር አለበት። ነገር ግን የተፈጥሮ ሀብት የተገኘበት ክፍለ ሀገር፣ የፈደራል መንግሥትን የክፍለ ሀገሩን የቀረጥ ታሪፍ ወሰን ሳይተላለፍ ማስከፈል አለበት።

## አንቀጽ 82

ተለይተው ስላልተሰጡ የታክስ እና የግብር ሥልጣኖች

1) በዚህ በሕገ-ኢትዮጵያ ተለይተው ያልተሰጡ ታክስና ግብር የመጣል ሥልጣኖችን በሚመለከት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ይወስናሉ፡፡ዝርዝር ጉዳይ በሕግ ይወጣል፡፡

አንቀጽ 83

የታክስና የግብር አጣጣል መርሆዎች

1. ክፍለ ሀገራትና የፌዴራሉ መንግሥት ታክስና ግብር በሚጥሉበት ጊዜ የሚጠየቀው ታክስና ግብር ከምንጩ ጋር የተያያዘና በአግባቡ ተጠንቶ የተወሰነ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
2. በመካከላቸው የሚኖረውን መልካም ግንኙነት የማይጐዳና ከሚቀርበው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. ለትርፍ የቆሜ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር ክፍለ ሀገራትና በፌዴራሉ መንግሥት ንብረት ላይ! የፌዴራሉ መንግሥትም በክፍለ ሀገራት ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ሥልጣን አይኖራቸውም፡፡

<u>አንቀጽ 84</u>

<u>የኢትዮጵያ የኦዲት ጀኔራል</u>

የኢትዮጵያ የኦዲት ጀኔራል በቀጥታ በሕዝብ በ14ቱም ክፍለ ሀገር ተወዳድሮ ለ4 አመት አገልግሎትና ለሁለት ዓመት ዙር ይመረጣል።

1) የኢትዮጵያ ኦዲተር ጄኔራል ለ4ዓመት አገልግሎት በቀጥታ ከ14ቱ ክፍለ ሀገራት ተወዳድሮ በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣል።
2) ዋናው ኦዲተር የፌዴራሉን የሚኒስቴርና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦች በመቆጣጠር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት፣ በበጀት ዓመቱ ለተሰሩት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን መርምሮ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3) ዋናው ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፡
4) የዋናው ኦዲተር ዝርዝር ተግባር በሕግ ይወሰናል፡፡

<u>አንቀጽ 85</u>

<u>የምርጫ ቦርድ</u>

1) በፌዴራልና በክፍለ ሀገራት የምርጫ ቦርድ ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለለተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል፡፡
2) ምርጫ ማጭበርበር በሕገ-ኢትዮጵያ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ በ15 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ የፈደራል መንግስት ወንጀል ነው። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
3) የምርጫ ቀን ማራዘም የሚቻለው፣ ሀ) በወረርሽኝ በሽታ ጊዜ፣ ለ) ሀይለኛ የአየር ችግር የመሣሰሉት ስከሰት፣ ሐ) የብሔራዊ ምርጫ ዘመቻ ለማድረግ ከዓቅም በላይ የሆነ አስቸጋሪ ነገር ስከሰት፣ አስራ አራቱም (15ቱም) የምርጫ ቦርድ ኮምሽነሮች ተስማምተው ለአገሪቱ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት በማመልከት ብሔራዊ ፍርድ ቤት አስራ አምስቱም (15ቱም) ዳኞች በድምፅ ብልጫ ካፀደቁ ማራዘም ይቻላል። ነገር ግን ብሔራዊ ምርጫ አስራ ሁለት (ከ12) ወራት በላይ ማራዘም አይቻልም።

<u>አንቀጽ 86</u>

<u>የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን</u>

1) የሀገሪቱን የሕዝብ ቁጥር በየጊዜው የሚያጠናና ቆጠራ የሚያካሂድ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ይኖራል፡፡ የኮሚሽኑ አባላት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
2) በብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ ውስጥ የየክፍለ ሀገሩ ነዋሪዎች ሕዝብ መካከል የዘር፣ የጎሳ ስም! እና የቀለም ልዩነት ለይቶ መቁጠር በሕገ-ኢትዮጵያ ፈጽሞ የተከለከለ ነው።
3) ኮሚሽኑ ዋና ጸሐፊ፣ አስፈላጊ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡
4) የኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ይጸድቃል፡፡
5) የሕዝብ ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ ይካሔዳል፡፡ በውጤቱም መሰረት የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሠረት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ይወስናል፡፡
6) የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት ነው፡፡ስለ ሥራው አፈጻጸም በየጊዜው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
7) ብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ የየክፍለ ሀገሩ ነዋሪዎች ሕዝብ ቁጥር መሠረት ያደረገ ብቻ ነው።

አንቀጽ 87

<u>የሕገ- ኢትዮጵያ</u>

<u>ማሻሻያ አሳብን ስለማመንጨት</u>

1) የሕገ- ኢትዮጵያ ማሻሻያ አሳብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በድምጽ ብልጫ የደገፈው፣ የሕዝብ ምክር ቤት በድምጽ ብልጫ የደገፈው ወይም ከሕዝብ ምክር ቤት አባል ክፍለ ሀገራት ውስጥ የክፍለ ሀገራት ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ የደገፉት ከሆነ ለውይይትና ለውሳኔ በመላው ሕዝብና መሻሻል ለሚመለከታቸው የክፍለ ሀገራት ይቀርባል፡፡

<u>አንቀጽ 88</u>

<u>ሕገ-ኢትዮጵያን ስለማሻሻል</u>

1) ሁሉም የክፍላተ ሀገር ሕዝብ የቀረበውን ማሻሻያ በድምጽ ብልጫ ሲያጸድቁት፣
2) ሁሉም የክፍላተ ሀገር ሕዝብ በሪፈሬንደም በድምጽ ብልጫ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት፣
3) ሕገ ኢትዮድያን ለማሻሻል ከኢትዮድያ ሕዝብ በስተቀር መንግስት ወይም የኢትዮድያ የሕዝብ ምክር ቤት ፈጽሞ ሥልጣን የላቸውም። ምክንቱም በመንግስት ሕግ ወይም በሕገመንግስትና ፣ በሕዝብ ሕግ ወይም የአገሪቷ የሕግ የበላይነት ሕግ፣ መካከል ትልቅ የሚለያቸው ቀይ መስመር በመካከላቸው ተቀምጧል። የኢትዮድያ የሕዝብ ምክር ቤት ሕገ መንግሥትን ሲያወጡ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ፣ሕገ ኢትዮድያ የሚፈቅድላቸውን ድንበር ጠብቀው አንድም ቃልም ሳይተላለፉ፣ ከሕግ የበላይነት ወይም ከሕገ ኢትዮድያ በታች ሆነው ለአገራችን ሕገ መንግሥትን እያወጡ ይቀጥላሉ። ምክንያቱም፣ ሕገ ኢትዮድያ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ ሁሉንም ዕኩል አድርጎ የሚገዛ የአገራችን የላዕላይ፣ ወይም የበላይ የኢትዮድያ የሕዝብ ኮንስትቱሽን ነውና።

<u>አንቀጽ 89</u>

<u>በሕገ- ኢትዮጵያ መሠረት የመገንጠል ጥያቄ ማንሳት ወንጀል ነው፡፡</u>

1) በፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ ሕገ-ኢትዮጵያ መሠረት 14ቱ ክፍለ ሀገራት በእኩልነት የጋራ ሀብት በጋራ የመጠቀም መብት ሕጉ ይደነግጋል፡፡እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር ዓመታዊ በጀት ድርሻቸውን የሚጋሩ ሲሆን የጋራ ሀብት አጠቃቀም የምነሳዉ ግጭት ብሄራዊ አንድነት

የምሽረሽር ሁነታ ሲያጋጥም በሕግ እና በጋራ ዉይይት ይፈታል፡፡ሆኖም ግን የህብት አጠቃቀም ግጭት ወደ መገጠል ጥያቄ ማንሳት በማንኛም መንግድ በሕግ አካታን የመገንጠል ጥያቄ የሚያስነሱ ድርጅቶች ቢኖሩ ወይም ቢፈጠሩ በሕገ-ኢትዮጵያን የተከለከለ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ወንጀል ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ 90</u>

<u>ስለ ከነማ ምርጫ (ከተማ ነዋሪዎች ማህበር)</u>

1) በሕገ- ኢትዮጵያ መሠረት በፌዴራል ዲሞክራትክ ሪፑብሊክ ኢትዮድያ ውስጥ ያሉት ትላልቅና ትናንሽ ከተሞች በክፍለ ሀገር፥ በአውራጃ፥ በወረዳ፥ በቀበሌ፥ እና በገበሬ ማህበራት ያለ ሕዝብ መሪውን ለ4 ዓመት በቀጥታ ሕዝቡ ይመርጣል።

## <u>አንቀጽ 91</u>

<u>ፌደራል ዲሞክራትክ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት</u> የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት ዓለም ዓቀፋዊ ደረጃ በጠበቀ መልኩ በአገራችን ላይ ለሚነሱ ችግሮች፣ በፍርድ ቤቶች መካከል ግጭቶች ቢነሱ፣ በአስተዳደርና በፍርድ ቤት መካከል ግጭት ቢነሳ፣ በፌደራልና በክፍለ ሀገር መካከል ችግር ቢነሳ፣ መንስኤውን በማጣራት አስፈላጊውን ውሳኔ በመስጠት ለጉዳዩ መፍተኼ የሚያስገኝ ሙሉ ሥልጣን ያለው ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው።

1) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሄራዊ ፍርድ ቤት በአገራችን ላይ በትልቁም ሆነ በትንሹ ከተቋቋሙት የብሔራዊ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የሚከሰቱትን የምርጫ መዛባት በማጣራት ለምርጫ መዛባት ተጠያቂ ለሆኑ ግለሰቦች ፕሬዝዳንትን ጨምሮ ጥፋታቸው በመረጃ ከተረጋገጠ በሕገ-ኢትዮጵያ ላይ በተደነገገው ምርጫ ማጭበርበር ወንጀል መሠረት የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ሙሉ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ የሕግ የበላይነትን የሚያስከብር የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሄራዊ ፍርድ ቤት ነው።
2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት በዋናነት በሚከተሉት የሕግ የበላይነት ጥሰት ላይ በማተኮር ለሚነሱ ችግሮችን መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ ለመስጠት ሙሉ ሥልጣን ያለው ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው። የኢትዮድያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት አራት አብይ ተግባሮች ይኖሩታል።
3) በፍርድ ቤቶችና በቢሮኪራሲ ላይ የሚነሱ ችግሮች ማቃለል፣

4) በፌደራል ፍርድ ቤትና በክፍለ ሀገር ፍርድ ቤት መካከል የሚነሱ ችግሮችን ማቃለል፣
5) በመደበኛ ፍርድ ቤትና በሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት መካከል የሚነሱ ችግሮችን ማቃለል፣
6) በክፍለ ሀገር አስተዳደርና በፌደራል መንግሥት መካከል የሚከሰቱ ችግሮችን የማቃለል ሙሉ ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው።
7) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት፣ በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ14ቱ ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 15 የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ከፍተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ያቀፈ ገለልተኛ ብሔራዊ ፍርድ ቤት ነው።
8) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መወዳደር ይችላሉ።

መመዘኛውም ፣ ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣ በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሥነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፣ ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ፣ተወዳዳሪዎች ሁሉ ሊቀመንበሩን ጨምሮ የሕግ ሙያ ያላቸው መሆን አለባቸው።

# አንቀጽ 92

## የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን

1) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን በሕገ-ኢትዮጵያ ውስጥ በምዕራፍ አንድ ላይ ከተደነገጉት ከሦስት ዋና የመንግሥት አካላት ፈጽሞ የተለየ በቀጥታ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ የሕዝብ ተወካዮችን የያዘ ከሦስቱም ዋና የመንግሥት አካል ጋር እኩል የሆነ ሙሉ ሥልጣን ያለው ነው።
2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን ለሀገራችን አሁን ላለውና ለሚመጣው ትውልድ ነፃና ገለልተኛ የሆነ! ከማናቸውም ፖለቲካ ድርጅት ግንኙት የሌለው! የሀገራችንን የሕግ የበላይነት ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ለማዋል! በአገራችን ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።
3) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን ማንኛውም የኢትዮጵያ ተወላጅ የተወለደበትና የሚኖርበት ሥፍራ ሁሉ የባለቤትነት ሙሉ መብት እንዳለው ለማስጠበቅ፣ በማንኛውም የኢትዮጵያ ተወላጅ ላይ የወገን! የጎሣ! የጾታ! የቀለም! እና የኃይማኖት ልዩነት ማድረግ በሕግ የሚያስቀጣ ዓለም ዓቀፋዊ ወንጀል መሆኑን የሚገልጽና የሚከታተል ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።

4) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን በሕጋችን ውስጥ በአንቀጽ (ሰማንያ ዘጠኝ 89) ላይ የተደነገገው በዋናነት ሥርዓታችን ዓለም ዓቀፋዊ የዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

5) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች ነፃና ገለልተኛ የሆነ በራሱ ሙሉ ሥልጣን ያለው በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ አምስት ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ኮሚሽኖችን ያቀፈ ሙሉ የመንግሥት አካል ነው።

እነሱም፣ 1) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣

2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣

3) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የኦዲት (የቁጥጥር) ኮሚሽን፣

4) የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣

5) የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ልማትና ዕድገት ወኪል ናቸው።

1) ይህ ኮሚሽን ከማናቸውም ከመንግሥት አካልና ከፖለቲካ ድርጅቶች ገለልተኛ የሆነ በቀጥታ በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጠ ከመንግሥት ዕኩል ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።

2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣የአገራችንን የሕግ የበላይነትን በሚመለከት ማንኛውንም ሕዝባዊ አገልግሎት፣ የመንግሥት ዋና መሥሪያ ቤቶች፣ የመንግሥት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች፣ የመንግሥት ወኪሎች፣እና ኮርፖረሽኖች፣ የአገሪቱ ፕረዝዳንትን ጨምሮ የሕግ የበላይነትን ተላልፈው ከተገኙ ተከታትሎ ኪስ በመመሥረት ማስቀጣት የሚችል በሀገራችን ውስጥ ትልቅ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ የሆነ የሕግ የበላይነት ኮሚሽን ነው።

3) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ በማዕከላዊነት ሆኖ ማንኛውንም ሕገወጥ ተግባራትን እየተቆጣጠረ፣ በተጨማርም ለሕዝባችን ስለዲሞክራሲ ዕውቀት እያስተማረ መሠረታዊ መብታችንን ከመንግሥትና ከመንግሥት ወኪሎች ሁሉ ማግኘት የሚገባንን ነገሮች በሙሉ በሕጋዊ መንገድ እንዲሟላ የደርጋል። በመቀጠልም በሕገ- ኢትዮድያ ውስጥ የተደነገጉትን የሰብዓዊ መበቶችና ጥቅሞች በሙሉ በሕጋዊ መንገድ እንዲሟሉ የደርጋል።

4) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ ማንኛውም የሕግ የበላይነት ጥሰቶች እንዳይታዩ ግልጽ የሆነ ተጠያቅነትና ኃላፊነት እንዲኖራቸው የማድረግ ሙሉ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ ኮሚሽን ነው።

5) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ በአገራችን ውስጥ ሁሉም የሀገራችን ዜጋ በማንኛውም የአገራችን ክፍል የመኖርና እኩል የሥራ ዕድል እንዲኖረውና ምንም ዓይነት ልዩነት እንዳይደረግበት ወኪሎችም ሆኑ፣ ዋና የመንግሥት መሥሪያቤቶችን ጨምሮ በሕግ ጥሰት የሚደርስ አድልዎ ለመቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ ኮሚሽን ነው።

6) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ14 ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 15 የሕዝብ ወኪሎችን ያቀፈ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።

7) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የሕዝብ አገልግሎት ኮሚሽን፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።

መመዘኛውም ፣

1) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣
2) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሰነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፣
3) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ፣

## <u>የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣</u>

1) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣ ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች ገለልተኛና ነፃ የሆነ፣ ማንኛውንም የሕግ የበላይነትን የሚመለከት ነገር ሁሉ የመቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።
2) የምርጫ መዛባት እንዳይኖረው የሚቆጣጠርና የምርጫ ጣቢያዎችን የሚያዘጋጅ ተመራጮችን የሚመዘግብ ከማዕከላዊ መንግሥት ገለልተኛ የሆነ ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን ዋና የሥራ ድርሻ፣

1) የሕግ የበላይነት ረቅቆች በብሔራዊ ሬፈረንደም ብቻ እንዲፀድቁ ያደርጋል።
2) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ምርጫ ጊዜ በቂ ፖሊስና በቂ ምስክሮችን በመመደብ የመቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን ያለው ከመንግሥት ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
3) ለምርጫ የተመዘገቡትን የፖለቲካ ድርጅቶችን ሕጋዊነታቸውን ያጣራል።

4) ብሔራዊ የፕሬዝዳንት ምርጫ ጊዜ ማጭበርበር እንዳይኖር ከዓለም ዓቀፋዊ ሕብረተሰብ ታዛቢዎችን ጨምሮ ጥብቅ የሆነ ቁጥጥር እንዲደረግ የማስፈጸም ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።
5) ምርጫ የማጭበርበር ጥፋት የተገኘበት አካል የአገሪቱን ፕረዝዳንት ጨምሮ፣ በሕገ- ኢትዮጵያ በአንቀጽ 82 ላይ በተደነገገው መሠረት ለፍርድ እንዲቀርብ ወደ ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት በአስቸኳይ ያቀርባል።
6) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣ በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ14ቱ ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 15 የሕዝብ ወኪሎችን ያቀፈ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
7) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የምርጫ ኮሚሽን፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።

መመዘኛውም ፤

1) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣
2) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሰነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፤
3) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ፣

## <u>የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን፣</u>

ይህ ኮሚሽን የፖለቲካ ቀውስ በአገሪቷ ላይ ሲከሰት በቂ ቁጥጥር በማድረግ፣ ማንኛውንም አካል የሕግ የበላይነት ምርጫ ወጭና ገቢ ሂሳብ መርምሮ የመንግሥት ወኪሎችን ሁሉ የአገሪቱን ፕሬዝዳንት ጨምሮ ተጠያቂ የሆነውን ክፍል ወደ ኢትዮድያ የሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል ሙሉ ሥልጣን ያለው ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።

<u>የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን በዋናነት የሚያከናወናቸው፣</u>

1) የመንግሥትና የሕዝብ ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ የሚደረግ ምዝበራ ቁጥጥር ለማድረግ ሙሉ ሥልጣን ያለው ኮሚሽን ነው።
2) ዓመታዊ የአገሪቷን ሂሳብ ሪፖርት ለሕዝብ ምክርቤት፣ ለኢትዮድያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤትና ለፕሬዝዳንት ያቀርባል።

3) የመንግሥት አሠራር ጥንካሬና ድካም ሪፖርት ያደርጋል፣ በሚድያም ለአገሪቱ ሕዝብ ግልጽ ያደርጋል።
4) በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ሥራ የተከናወኑትን የሂሳብ ሰነዶች አጠናቅሮ ሪፖርት ያቀርባል።
5) ማንኛውንም የተዛባ የአሠራር ወንጀል በ60 ቀን ውስጥ አጠናቅሮ ለኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤትና ለመደበኛ ፌደራል ፍርድ ቤት ያቀርባል።
6) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ14 ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 15 የሕዝብ ወኪሎችን ያቀፈ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
7) የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የቁጥጥር ኮሚሽን የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።

<u>መመዘኛውም</u> ፣

1) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣
2) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሰነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፣
3) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ ፣

<u>የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣</u>

1) የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ ከመንግሥትና ከፖለትካ ድርጅቶች ነጻና ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።
2) የኢትዮድያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ሥልጣን በአገራችን ውስጥ ዓለም ዓቀፋዊ ሰብዓዊ የመብት ጥሰትን ከዓለም መንግሥታትና ከአገራችን የሕግ የበላይነት ብሔራዊ ፍርድ ቤት ጋር በመተባበር ሰብዓዊ የመብት ወንጀሎችን በመከታተል ሪፖርት ያቀርባል።
3) በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሰብዓዊ መብታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ከዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር አገራችንን ወክሎ የሚሠራ ነፃና ገለልተኛ ኮሚሽን ነው።
4) ለሰብዓዊ መብት ጥሰት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሕጋዊ ፍርድ እንዲያገኙ ይሠራል።
5) እስር ቤቶች ለሰው ልጅ አመቺ ሳይሆን የቅጣት ሥፍራ እንዲሆን ተደርገው የተሰሩትን ይቆጣጠራል።
6) የሰብዓዊ መብት ጥሰት ጉዳይ መረጃው ትክክለኛ መሆኑን ያጣራል።

7) ሰብዓዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው ግለሰቦችን ጉዳይ በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡና ተገቢውን ካሣ ለግለሰቡና ለቤተሰቦቻቸው ጭምር እንዲከፈላቸው ያደርጋል።

8) ከዓለም ዓቀፍ ሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ኮሚሽን ጋር የተሳሰረ ግንኙነት በመፍጠር የኢትዮጵያ መንግሥት በሕዝባችን ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወንጀል ከፈጸመ በዓለም ዓቀፋዊ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ሕጋዊ ፍርድ እንዲያገኝ ያደርጋል።

9) ያለ በቂ መረጃ ማንም የኢትዮድያ ዜጋ እንዳይከሰስ በአገራችን ውስጥና በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮድያውያን ሁሉ ሙሉ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል።

10) የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በአንድ ሊቀመንበር የሚመራ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ14 ክፍለ ሀገር በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጡ 15 የሕዝብ ወኪሎችን ያቀፈ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ነው።

11) የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።

መመዘኛውም ፣

1) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣

2) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሰነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፣

3) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ መሆን አለባቸው።

# የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ልማትና ዕድገት ኮሚሽን፣ (15 )

1) ለመላው ኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ልማት ዕኩል መዳረሱን ይቆጣጠራል። የትምህርት፣ የጤና፣ የውኃ፣ የእርሻ፣ የመንገድ፣ ለአነስኛ ገቢ ቤተሰብ ነፃ የመኖሪያ ቤቶች ዕኩል ለሁሉም ክፍለ ሀገር መዳረሱን ይቆጣጠራል።

2) የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ልማትና ዕድገት ወኪል የአገልግሎት ዘመናቸው ለስምንት ዓመት ሲሆን እንደገና ለመመረጥ በየስምንት ዓመት መፎካከር ይችላሉ።

መመዘኛውም ፣

1) ዕድሜ ከ35 ዓመት በላይ፣

2) በሕዝብ አስተዳደር መልካም ሰነ ምግባርና በሥራው መልካም ውጤት ያስገኘ መሆኑ የተመሰከረለት ፣

3) ከመንግሥትና ከፖለቲካ ድርጅቶች አካል ነጻ የሆነ መሆን አለባቸው።

## አንቀጽ 93

## የፌደራል መንግስት ፕሬዝዳንት፣ወይም የክፍላተ ሀገር አስተዳዳሪዎች ወንጀል፣

1) ሏዓላዊ ሀገራችንን አካል ቆርጦ፣ ወይም ቆርሶ መስጠት፣ ወይም ለጦርነት ከጠላት ጋር በመሻረክ ሀገርን ማስወጋት ወንጀል ከፈፀሙ፣

2) በሕገ ኢትዮድያ መሠረት፣ ፕሬዝዳንትና የፌደራል መንግስት ሠራተኛ፣ ወይም የሕዝብ ምክር ቤት አባል፣ ወይም የክፍለ ሀገር ዋና አስተዳደሪ፣ ለጦርነት አገራችንን ለማስወጋትና፣ ወይም የኢትዮድያን አካል መሬት ቆርጦ ለውጭ ጠላት ለመስጠት፣ እና የተፈጥሮ ሀብቷን በስውር በምስጥር ለመሸጥ ከውጭ ጠላት ጋር ተስማምቶ በማስረጃ ከተረጋገጠበት/ከተረጋገጠባት፣ ፕሬዝዳንት፣ የዕድሜ ልክ እሥራት መቀጣት አለበት። ማንኛውም የፈደራል መንግስት ሠራተኛ፣ የሕዝብ ምክር ቤት አባል፣ ወይም የክፍላተ ሀገር ዋና አስተዳዳሪ፣ በማስረጃ ከተያዙ የሁሉም ቅጣት 10 አመት ፅኑ እስራትና 500,000 የኢትዮድያ ብር መቀጣት አለባቸው።

## ሙስና ወይም ጉቦ የፈዴራል መንግስት ወንጀል ስለመሆኑ

3) ለሕዝብ አገልግሎት ለፈደራልና ለክፍላተ ሀገር ደረጃ የተሰማሩ ሁሉ ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ጨምሮ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሠሩ ባለስልጣናት በሙሉ የሙስና ወይም የጉቦ ወንጀል በመፈፀም የተረጋገጠባቸው ሁሉ የተሰጣቸው ስልጣንና የሥራ ዕድላቸውን ያጣሉ። በተጨማሪም በእስራት መቀጣት አለባቸው።

4) ከፕሬዝዳንት ጀምሮ፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ካብኔቶች፣ አምባሳደሮች፣ መላው ስቭል የሕዝብ አገልግሎት ሠራተኞች በሙሉ ማንኛውንም ስጦታ መቀበልና ሴት ልጅን በስልጣናቸው በሥራዋ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ ፈፅሞ የተከለከለና በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው።

5) የሙስና ወይም የጉቦ ወንጀሎች ቅጣት ከፕሬዝዳንት ጀምሮ ማንኛውም የሕዝብ አገልግሎት ሠራተኞች በፍርድ ቤት ከተረጋገጠባቸው ከሥራቸውና ከሥልጣናቸው ይሰናበታሉ። ከፕሬዝዳንት ጀምሮ ማንኛውም የሕዝብ አገልግሎት ሠራተኞች የሙስና ወይም የጉቦ ወንጀል በፍርድ ቤት ከተረጋገጠባቸው እስከ 13 ዓመት በፅኑ እስራት መቀጣት አለባቸው።

6) በሕገ ኢትዮድያ፣ በሕገወጥ መንገድ በኢትዮድያ ውስጥ፣ ወይም ከኢትዮድያ ውጭ የኢትዮድያን ገንዘብ በማጭበርበር ማተም፣ ወይም ፎርጅድ ማሳተም፣ 5 መቶ ሚልዮን ብር (500 million Birr) ፣ ወይም 25 ዓመት በፅኑ እስራት ያስቀጣል።

## የኢትዮድያ የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር

7) የኢትዮድያ የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር ነፃና ገለልተኛ ሙሉ ሥልጣን ያለው አካል ነው። የኢትዮድያ የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር ዋና የሥራው ተግባር፣ የሕዝብ ምግብና የእንስሳት ምግብ ጥራትና ጤንነት በጥብቅ መቆጣጠር ነው።

8) የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር የሚሾመው በእውቀታቸውና በችሎታቸው ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ምክር ቤት ቀርበው በመመዝገብ ከፍተኛ የድምፅ ብልጫ ያገኘ ወይም ያገኘች ዕጩ ተመራጭ ይሆናል።

9) የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር ማንኛውንም የሕዝብ ምግብ፣ በተለይ ሱስ የሚያስይዙ የጤና ጠንቅ የኮንትሮባንድ መድኃኒቶች በጥብቅ ይቆጣጠራል። የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት በመጣስ በምግብና በመድኃኒት ላይ ወንጀል ሠርተው በሕዝብና በእንስሳት ላይ ጉዳት ያደረሱ ወንጀለኞች ተከሳሾች ሁሉ በ15 ዓመት ፅኑ እስራትና ከ2 ሚሊዮን እስከ 5 (አምስት) ሚሊዮን ብር መቀጣት አለባቸው።

## አንቀጽ 94

## የመዘዋወር መብትና በየመንገድ ያሉ የፍተሸና የቁጥጥር ኬላዎችን ስለመከልከል

1) በሕገ ኢትዮጵያ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ፈለገበት አከባቢ ያለ አንዳች ፍተሻ ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋውሮ ለመስራት፣ ለመኖር፣ ለመማር፣ ለመነገድ፣ ሙሉ መብት አለው።

2) በሕገ ኢትዮጵያ በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ የመሬት ድንበር መፍጠር፣ በአገር ውስጥ በማንኛውም ስፍራ መገናኛ መንገዶች ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥርና የፍተሻ ጣቢያ ኬላዎችን መፍጠር፣ በየመንገዱ የሸቀጥ ዕህል፣ ቡና፣ ማንኛውም ምርት

በፈደራልና በክፍላተ ሀገር መንግስት ምንም ዓይነት እገዳ እንዳይደርግ በሕገ ኢትዮድያ  በጥብቅ የተከለከለ ነው።

# አንቀጽ 95

# የምግብና በቂ የመኖሪያ ቤት ዋስትና

1) በሕገ ኢትዮድያ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰብና ግለሰቦች፣ ቤት አጥዎች፣ በጎዳና ላይ ተዳዳሪዎች፣ ረዳትና በቂ ገቢ የሌላቸው ለአቅመ አዳም የደረሱ ወጣቶች፣ ያለአንዳች ልዩነት  የበቂ መኖሪያ ቤት ዋስትና የፈዴራልና የክፍላተ ሀገር መንግስት ለሁሉም በዕኩልነት የማዳረስ ግዴታ አለባቸው።

2) የበቂ ምግብ ዋስትና የፈዴራልና የክፍላተ ሀገር መንግስት ለሁሉም በዕኩልነት የማዳረስ ግዴታ አለባቸው።

3) አድሱ የኢትዮድያ የሕግ የበላይንት (ሕገ ኢትዮድያ)፣ በኢትዮድያ ውስጥ ሁሉም የኢትዮድያ ሕዝብ በቂ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት ይሰጣል። በቂ  መኖሪያ ቤት የሚሰጥበት ዋናው ምክንያት፥

1)  በሚልዮን የሚቆጠር የኢትዮድያ ሕዝብ የፍትሕ ዕጦትና መንግስት በፈጠረው ጦርነት ምክንያት ከቤት ንብረቱ ተፈናቅሎ ስለሚገኝ ነው። ይህ ዕርዳታ በዘላቅነት

ግብ እንድመታ፣ በተከኒክና በገንዘብ ወጪ ፕሮግራም ወይም (Trust Fund) መደጎሚያ በጀት ፕሮግራም ከአሜርካ (USAID) ተራድዖ ድርጅትና ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር የሒሳብ ቁጥር ተከፍቶ ለመላው ኢትዮድያ ሕዝብ ቅድሚያ ለተፈናቃይ ሕዝብ በመስጠት ያከናውናል፣ ለቀጣዩ ትውልድም ይህ ሕግ በቋምነት ያገለግላል።

2) በአድሱ የኢትዮድያ የሕግ የበላይነት (ሕገ ኢትዮድያ) መሠረት፣ ሁሉም የኢትዮድያ ሕዝብ በቂ የመኖሪያ ቤት ያለ አንዳች አድልዎ በዕኩልነት የማግኘት ሙሉ መብት ስለሆነ፣ ከሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው መሠረታዊ መብት መሆኑን ይገልጻል።

3) የኢትዮድያ ሕብረተሰብ የኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተቀዳሚ ተግባሩ፣ ለኢትዮድያ ሕዝብ በ14ቱም ክፍላተ ሀገር ላለው በዕኩልነት በተለይ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት ቅድሚያ በመስጠት በቂ የመኖሪያ ቤት ለሁሉም ኢትዮድያዊ በዕኩልነት መዳረሱን ያረጋግጣል። ምክንያቱም፣ በቂ የመኖሪያ ቤት ለኢትዮድያ ሕዝብ በዕኩልነት ማዳረስ፣ በኢትዮድያ ውስጥ የድህነት ቀንበር ለመስበር፣ ወይም የድህነት ምንጭ ለማድረቅ ይረዳል። ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት፣ ቤት ማለት፣ ጣራና ግድግዳ ብቻ ሣይሆን፣ ብዙ የቤተሰብ ሕይወት የያዘ ክፍል ስለሆነ ነው።

4) በቂ የመኖሪያ ቤት ጉዳይ በዓለም ዓቀፍ ልማትና እድገት ኮሚቴ ዓላማ የሚለው፣ "የአንድ ሕብረተሰብ እድገቱ፣ ባህሉ፣ ሠላሙ፣ ክብሩ፣ ተጠብቆ መኖር የሚችለው፣ በቂ የመኖሪያ ቤት ሲኖረው ብቻ ነው"፣ በማለት ስለሚያምን ነው። ስለሆነም፣ አድሱ

የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት (ሕገ ኢትዮጵያ) ዋናውና መሠረቱ፣ በቂ የመኖሪያ ቤት በመንግስት በኩል ለሁሉም በዕኩልነት ማዳረስ መቻል፣ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድነትን፣ ሠላምን፣ ዕድገትንና ዕኩልነትን ማምጣት ብቻ ሣይሆን፣ የግለሰብና የቤተሰብ ሕይወት ይቀይራል ብሎ ስለሚያምን ነው።

5) በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በቂ የመኖሪያ ቤት እንድኖረው ሕገ ኢትዮጵያ የወሰነበት ዋና ዓላማ፣ የዓለም ዓቀፍ የቃል ኪዳን ሕግ አንቅጽ 17 መሠረት ሁሉም ሰው በአገሩ ቤት ማግኘት የሰው ልጅ መሠረታዊ መብት ነው ይላል። ቀጥሎም፣ የአንድ ሰው ቤትና የቤተሰብ ሕይወት የተቆራኘ ስለሆነ መንግስት ማንኛውንም ሕገወጥ ድርግት በቤትና በቤተሰብ ላይ እንዳይደርስ መጠበቅ አለበት ስለሚል፣ ኢትዮጵያም የዚህ የቃል ኪዳን አባል ሆና ያፀደቀችውና የፈረመችው እ/አ/አ/ ሰኔ 11/ 1993 ዓም ስለሆነ፣ የዓለም ዓቀፋዊ ግዴታዋን መፈፀም ግዴታ ስለሆነ ነው።

6) በኢትዮጵያ ውስጥ አድሱ የሕግ የበላይነት (ሕገ ኢትዮጵያ) በረፈረንደም የኢትዮጵያ ሕዝብ ካፀደቀ በኋላ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኪራይም ሆነ በባለቤትነት ከሚኖርበት ከመኖሪያ ቤት መንግስት በቂ አማራጭ ሣይሰጠው ማስወጣት፣ ማፈናቀል፣ በከፍተኛ ወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር ነው። ይህንን ወንጀል ፈጽመው የተገኘ ግለሰብ፣ ወይም የመንግስት አካል፣ ያለ ፍርድ ቤት ውሳኔ የፈፀመ ሁሉ ቤቱን በውርስ ለመንግስት ያስረክባል። የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ኢኮኖሚክ ዕድገትና

ልማት ኮሚሽን ቢሮ በከፍተኛ ደረጃ ይህ ወንጀል እንዳይፈፀም በ14ቱም ክፍላተ ሀገር ጥብቅ ቁጥ ጥር ማድረግ አለበት።

7) የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ኢኮኖሚክ ዕድገትና ልማት ኮሚሽን ቢሮ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በ14 ቱም ክፍላተ ሀገር ያለ ሁሉ አንዳች አድልዖ ሣይደርስበት በቂ የመኖሪያ ቤት እንድዳረስና ተግባራዊ ለማድረግና፣ የገንዘብ ወጭ ለመቆጣጣር፣ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ኢኮኖሚክ ዕድገትና ልማት ኮሚሽን፣ የዓለም ባንክ፣ የአሜርካ ተራድዖ (USAID)፣ የሕግ ጠበቃዎች፣ አንድ ላይ ሆነው በመነሻ ካፕታል $5 million (አምስት ሚልዮን የአሜርካን ዶላር) Trust Fund ተቀማጭ በማድረግ በዓለም ባንክ ውስጥ የሂሳብ ቁጥር ይከፈታል። የወጭ ሰነድ በሙሉ በውጭ ኦዲቴር (external auditor) እየተቆጣጠረ ሥራው በትክክል መከናወን አለበት።

8) በኢትዮጵያ ውስጥ አድሱ የሕግ የበላይነት (ሕገ ኢትዮጵያ) በረፈረንደም የኢትዮጵያ ሕዝብ ካፀደቀ በኋላ በቤቶች ላይ የሚደረግ ብልሹ የቤት ኪራይ ሥርዓተ ዐልባኝነት ለማስወገድና የሁሉም ኢኮኖሚ መሬት ነክቶ እንድነሳ አገር ዓቀፋዊ የቤት ኪራይ፣ የአፓርትሜንት ኪራይ፣ እና፣ የሆቴሎች አልጋ ኪራይ፣ በሚከተለው የዋጋ ገደብ በዝርዝር አስቀምጠዋል።

I) ባለአንድ መኝታ ቤት ወይም አፓርትሜንት ኪራይ በወር፣ 100.00 ብር (አንድ መቶ የኢትዮጵያ ብር).

2) ባለሁለት መኝታ ቤት ወይም አፓርትሜንት ኪራይ በወር፣ 200.00 ብር (ሁለት መቶ የኢትዮጵያ ብር).

3) ባለሦስት መኝታ ቤት ወይም አፓርትሜንት ኪራይ በወር፣ 300.00 ብር (ሦስት መቶ የኢትዮጵያ ብር).

4) ባለአራት መኝታ ቤት ወይም አፓርትሜንት ኪራይ በወር፣ 400.00 ብር (አራት መቶ የኢቶዮጵያ ብር) እንድሆን በሕግ ተገድበዋል።

5) የችርቻሮ አደራሽ ኪራይ በካሬ ሜትር በወር፣ 3.50 ብር (ሦስት የኢትዮጵያ ብር ከሃምሳ ሣንቲም) መብለጥ የለበትም።

6) የቢሮ ቦታ ለመከራየት በካሬ ሜትር በወር፣ 3.00 ብር (ሦስት የኢትዮጵያ ብር) መብለጥ የለበትም።

7) ማንኛውም ሆተል ለመከራየት ባለ5 ኮከብ ጨምሮ ለኢትዮጵያ ዜጋ የአልጋ ዋጋ ለአንድ ሌሊት፣ 125.00 ብር (አንድ መቶ ሃያ አምስት የኢትዮጵያ ብር)፣ መብለጥ የለበትም።

8) ለውጭ ዜጋ ሆተል ለመከራየት ባለ 5 ኮከብ ጨምሮ የአልጋ ዋጋ ለአንድ ሌሊት፣ 375 ብር (ሦስት መቶ ሰባ አምስት የኢትዮጵያ ብር) መብለጥ የለበትም።

9) በአድሱ የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት (ሕገ ኢትዮጵያ) መሠረት ቤት ወይም አፓርትሜንት በኢትዮጵያ ውስጥ በውጭ ገንዘብ ለደንበኞች ማከራየት ፈጽሞ በሕግ የተከለከለ ነው።

10) በአድሱ የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት (ሕገ ኢትዮጵያ) መሠረት፣ በአገር ውስጥና በመላው ዓለም ላይ በስዴት ተበትኖ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ፣ በአንቀጽ 8 መሠረት: 2 (ሁለት) የዜግነት መብት ማግኘት አለበት ይላል። ስለሆነም፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖር ሁሉ፣ ለቤቱም ሆነ ለመሬቱ ሕጋዊ ግብሩን ለአገሩ ለኢትዮጵያ እየከፈለ፣ የአገሩ ድርሻ ዕኩል እንዲካፈል፣ በአገር ውስጥ ይሁን በውጭ አገር የሚኖር ሁሉ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በመረጠው ከተማ ውስጥ፣ ከኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባን ጨምሮ፣ 6,000ሺ (ስድስት ሺ) ካሬ ሜትር የግል መኖሪያ ቤት ለመሥራት ኢትዮጵያዊ ማንነቱን በበቂ መረጃ ያቀረበ ሁሉ፣ ነጻ መሬት የማግኘት ሙሉ መብት አለው። ይህንን ዕድል በማጭበርበር የተያዙ ግለሰቦች፣ በ14 ቱም ክፍላተ ሀገር ስማቸው ተጣርቶ ወንጀሉ ከተገኘባቸው፣ ከፍተኛ ቅጣት መቀበል አለባቸው።

11) በአድሱ የኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት (ሕገ ኢትዮጵያ) መሠረት፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው፣ የግል ቤት የሌላቸው፣ አካለ ስንኩላን፣ አረጋውያን፣ ተምረው ሥራ የሌላቸው ወይም ያላገኙ ወጣቶች፣ በቂ የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ፣ የፌደራል፣ የክፍላተ ሀገር፣ ሁሉም የኢትዮጵያ ከተማዎች አስተዳደር፣

ዋናው የመንግስት ሥራ አካል፣ የቤት ፈላጊዎችን በየከተማው በዝርዝር መዝግቦ ይህንን ሕግ በትክክል በተግባር ላይ የማዋል ግዴታ አለባቸው።

12) በአድሱ የኢትዮድያ የሕግ የበላይነት (ሕገ ኢትዮድያ) ዋና ዓላማው፣ የኢትዮድያ ሕዝብ፣ በገዛ ሀገሩ በምግብና በመኖሪያ ቤት እጦት፣ የሚሰቃዩትን ግለሰቦችና ቤተሰቦች ሕይወት መቀየር ስለሆነ፣ ከእንግዲህ የሚመጣ የኢትዮድያ መንግስት ያለ አንዳች አድልዖ፣ ለሁሉም ዕኩል በሆነ መንገድ ለማገለገል፣ ለሕገ ኢትዮድያ ወይም፣ ለሕዝብ ሕግ፣ መታዘዝ ግዴታቸው መሆኑን አምነው መቀበል አለባቸው። ይህ ማለት፣ በኢትዮድያ ውስጥ ከእንግዲህ ወዲህ፣ ረሃብን፣ የመኖሪያ ቤት እጦትን፣ በበረንዳ ላይ ወይም በጎዳና ላይ መውደቅን፣ ፈጽሞ ከኢትዮድያ ምድር ለማስወገድ፣ ከእንግዲህ የሚመጣ የኢትዮድያ መንግስት ለአድሱ ለኢትዮድያ ሕግ ወይም ለሕዝብ ሕግ፣ (ለሕገ ኢትዮድያ) ፕሬዝዳንትን ጨምሮ፣ የግድ መታዘዝ አለባቸው ማለት ነው።

## አንቀጽ 96

## ነፃ የትምህርት ዋስትና

1) በሕገ ኢትዮድያ ሁሉም ኢትዮድያዊ መካከለኛ ገቢ ያላቸው፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦችና ግለሰቦች በሙሉ፣ በነፃ የመማር ሙሉ መብት አላቸው።

2) በሕገ ኢትዮጵያ ሁሉም ኢትዮጵያዊ መካከለኛ ገቢ ያላቸው፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦችና ግለሰቦች በሙሉ፣ ከመዋለ ሕጻናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ቤት ድረስ፣ በነፃ እንድማሩ የፈዴራልና የክፍላተ ሀገር መንግስት ግዴታ አለባቸው።

3) ወላጆች ሁሉ ሕፃን ነፃ የትምህርት ዕድል እንዲያገኝ ሙሉ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

4) በሕገ ኢትዮጵያ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከመሃይምነት ነፃ መሆን አለበት። የኢትዮጵያ መንግስትም ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት።

5) በሕገ ኢትዮጵያ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዕደጥበብ፣ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በፈጠራ ሙያ፣ በስፖርት፣ ለበለፀጉ ግለሰቦችና ወጣቶች በመንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ በዕኩልነት ያለአንዳች ልዩነት የፌደራልና የክፍላተ ሀገር መንግስት በቂ ድጋፍ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

## አንቀጽ 97

## ነፃ የጤና ሕኪምና ዋስትና

1) በሕገ ኢትዮጵያ ሁሉም ኢትዮጵያዊ መካከለኛ ገቢ ያላቸው፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦችና ግለሰቦች በሙሉ፣ በነፃ የጤና ሕኪምናና ከፌደራልና ከክፍላተ ሀገር መንግስት እንክብካቤ ሁሉም በዕኩልነት የማግኘት መብት አላቸው።

2) በሕግ ኢትዮጵያ የፌደራልና የክፍላተ ሀገር መንግስት ለሥራ አጦች፣ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች፣ ለነፍሰ ጡሮች፣ ለአረጋውያን፣ ለአካለ ስንኩላን፣ ለመዋለ

ሕጻናት፣ ለጡረተኞች፣ ለሁሉም የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ያለ አንዳች ልዩነት ሙሉ ድርሻቸውን ማግኘት አለባቸው።

3) በሕግ ኢትዮድያ የፌደራልና የክፍላተ ሀገር መንግስት ሁሉም የከተማ አስተዳደር፣ ለመካከለኛና አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦችና ግለሰቦች፣ ነፃ የጤና ሕክምና ዋስትና ለኢትዮድያ ዜጋ ሁሉ በዕኩልነት ያለ አንዳች ልዩነት በየደረጃው ላለው ለኢትዮድያ ሕዝብ በሙሉ የፌደራልና የክፍላተ ሀገር መንግስት እንዲሁም ሁሉም የከተማ አስተዳደር፣ ተግባራዊ የማድረግ ሙሉ ግዴታ አለባቸው።

## አንቀጽ 98

## የኢትዮድያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም

ሕገ ኢትዮድያ እስፖርት ለሰውነት ጤንነት ጠቃሚ በመሆኑ ማንኛውም ኢትዮድያዊ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ወገን፣ የአካል ጉዳተኛነት፣ ሣይገድባቸው  የኢትዮድያ መንግስት ሁሉም የኢትዮድያ ዜጋ በዕኩልነት መሳተፍ የሚችልበት መንገድ በማመቻቸትና፣ በተጨዋቾች፣ በሯጮች፣ እና በአሰልጣንኞች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንድደግፋቸውና፣ ምንም ዓይነት አድልዎ፣ ተፅኖ፣ ወገንተኝነት፣ እንዳይደረግባቸው ለመቆጣጠር  ይህ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት: የኢትዮድያ እስፖርት ፌደርሽንን  ለመቆጣጠር ; ገለልተኛ ተቋም በሕግ የበላይነት ሥር ተቋቁሟል።

1) የኢትዮድያ እስፖርት ኮሚሽን ፈጽሞ ከአሺሽ የነጻ እንዲሆን፣ ለሁሉም ኢትዮድያዊ ዕኩል የመሳተፍ ዕድል ማግኘታቸውን ይህ ተቋም በጥብቅ መቆጣጠር አለበት።

2) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም በብሔራዊ፣ በክፍላተ ሀገር፣ በከተማና፣ በገጠር ላሉ ለኢትዮጵያ ልጆች ዕኩል የእስፖርት ተሳትፎ ዕድል ማግኘታቸውን ይቆጣጠራል።

3) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም ፍትሐዊ፣ ብሔራዊ፣ የሁሉም የኢትዮጵያዊ ዜጋ ዕኩል ተሳትፎ እንድያገኝ ከብሔራዊ እስከ ክፍላተ ሀገር እስፖርት ክለቦችን፣ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ትምህርት ቤቶችን ተሳትፎና አስተዳደር ይቆጣጠርል።

4) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም ፍትሐዊ፣ ብሔራዊ፣ የሁሉም የኢትዮጵያዊ ዜጋ ዕኩል ተሳትፎ እንድያገኝ ከብሔራዊ እስከ ክፍላተ ሀገር እስፖርት ክለቦችን፣ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ትምህርት ቤቶች ተሳትፎ፣ በአጭርና በረጅም ሩጫ፣ በኳስ፣ በትራክ ሩጫ፣ በባስኬት ኳስ፣ በቮልቮል ኳስ ጨዋታ፣ በቦክሲንግ፣ በውኃ ዋና፣በተንስ ኳስ፣ በብስክሌት ሩጫ፣ ለመሳተፍ አቅም ለሚያንሳቸው ወጣቶች፣ የመንግስት ዕርዳታ ዕኩል መዳረሱን በጥብቅ ይቆጣጠራል።

5) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም ፍትሐዊ፣ ብሔራዊ፣ የሁሉም የኢትዮጵያዊ ዜጋ ዕኩል ተሳትፎ እንድያገኝ ከብሔራዊ እስከ ክፍላተ ሀገር እስፖርት ክለቦችን፣ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ትምህርት ቤቶች፣ በቀበሌና፣ በገበሬ ማህበር ደረጃ፣ ያሉ መሪዎች፣ በየአራት ዓመት በሕዝብ ይመረጣሉ። ሆኖም ያለጊዜ ገደብ እንደገና በየአራት ዓመት የመወዳደር ዕድል አላቸው።

6) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም፣ የክሌቦች ምዝገባ፣ የተጨዋቾች አመራረጥ ፍትሐዊነት፣ የማራቶን ሯጮችና፣ የአሰልጣኞች ፍትሐዊ አመራረጥና፣ በመካከላቸው የሚፈጠሩ ችግሮች፣ በሕጋዊ መንገድ እንዲፈቱ ዋስትና ለመስጠት የተቋቋመ ተቋም ነው።

7) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም፣ የክሌቦች ምዝገባ፣ የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽንን በበላይነት ለመቆጣጠር፣ የገቢና ወጭ ብኩንነት ለምቆጣጠር፣ በአሰልጣኞችና  በተጨዋቾች ላይ የሚደርሰውን ተፅዕኖ ተቆጣጥሮ ለመቅጣት ወይም ወደ ፍርድ ቤት ለማቅረብ የተቋቋመ ተቋም ነው።

8) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም፣ በዋናነት በሁሉም ደረጃ እስፖርተኞች ውስጥ ምንም ዓይነት አሺሽ እንዳይገኝ፤ ምንም ዓይነት አድልዎ፤ እንዳይደረግ፣ የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽንን በበላይነት ለመቆጣጠር የተቋቋመ ገለልተኛ ተቋም ነው።

9) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም፣ ለተጨዋቾችና፣ ለአሰልጣኞች ምንም ዓይነት አድልዎ እንዳይደረግ፣ በሁሉም ደረጃ ዕኩልና ፍትሐዊ መሆኑን ለማረጋገጥና፣ የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽንን በበላይነት ለመቆጣጠር የተቋቋመ ገለልተኛ ተቋም ነው።

10) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም፣ የኢትዮጵያ እስፖርት ፌደረሽን፣ ማንኛውም ጥፋት ከተገኘበት፣ ወደ  ፌደራል ፍርድ ቤት፣ ወይም ወደ

ሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት  በማቅረብ ለማስቀጣት የሚችል ሙሉ ሥልጣን ያለው አካል ነው።

11) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም፣ የኢትዮጵያ እስፖርት ፌደረሽን፣ ማንኛውም ጥፋት ከተገኘበት፣ ወደ ፌደራል ፍርድ ቤት፣ ወይም ወደ ሕግ የበላይነት ፍርድ ቤት  በማቅረብ የእስፖርት ፌደረሽን ባለሥልጣናት በጥፋታቸው በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ፣ በአምስት ዓመት እስራትና፣ ከሶስት መቶ ሺህ (300,000) እስከ አምስት መቶ ሺ (500,000) ብር ቅጣት፣ እና፣ የሥራ ፍቃዳቸው እንዲቀሙ፣ ተመልሰውም የመንግስት ሥራ  እንዳያገኙ ማድረግ የሚችል ሙሉ ሥልጣን ያለው አካል ነው።

12) የኢትዮጵያ እስፖርት ኮሚሽን ገለልተኛ ተቋም፣ አንድ ሊቀመንበርና፣ አስራ አራት ኮሚሽነሮች፣ ከአስራ አራቱም ክፍላተ ሀገር በሕዝብ የተመረጡ ሆነው፣ ለአራት ዓመት ያገለግላሉ። ሆኖም፣ በየአራት ዓመት ለመወዳደር ይችላሉ። የጊዜ ገደብም የለባቸውም።

መመዘኛ፥

ሀ) በአገር ውስጥ ወይም በውጭ የተወለዱ፣

ለ) ዕድሜ፥ 35 ዓመት በላይ፣

ሐ) ከመንግስት ሥራ ነፃ የሆኑ፣

መ) ከመንግስትና፣ ከፖለትካ ፓርትዎች፣ በውስጥና በውጭ አባል ያልሆኑ መሆን አለባቸው።

## አንቀጽ 99

### የመጨረሻ ሕጋዊ እውቅና ስላለው ቅጂ

1) ሕገ ኢትዮጵያ በሁለቱም በአማርኛና በእንግልዘኛ የተደነገጉት ሕጎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ብልጫ በረፌረንደም ከጸደቀበት ስዓት ጀምሮ በአገራችን ላይ የመጨረሻ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ሰነድ ይሆናል።

2) ሕገ ኢትዮጵያ በሁለቱም በአማርኛና በእንግልዘኛ የተደነገጉት ሕጎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ብልጫ በረፌረንደም ከጸደቀበት ስዓት ጀምሮ በአገራችን ላይ ፕሬዝዳንቱን ጨምሮ ሁሉም ሰው ከሕግ የበታች ነው።

3) ሕገ ኢትዮጵያ በሁለቱም በአማርኛና በእንግልዘኛ የተደነገጉት ሕጎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ብልጫ በረፌረንደም ከጸደቀበት ስዓት ጀምሮ በምድራችን ላይ ከሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ ነው፡፡

4) የሚቀጥለው ትውልድ ሕገ ኢትዮጵያን በሕዝብ ድምፅ ብልጫ ያሻሽል እንጂ በፍጹም መሻር የለበትም።

**የእግዚአብሔርን ቃል እናስታውስ!!**

**የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር።**

**አሞፅ (፱ ፥፯)**

**በቅዱስ ቁርዓን ነብዩ መሃመድ፤ ኢትዮጵያን አትንኳት ይላል።**

# በሕገ ኢትዮጵያ ረቂቅ ላይ ተሳታፊዎች ፤

# ሕገ ኢትዮጵያ (The Ethiopian Constitution)

***የመጀመሪያ ረቂቅ ፀሐፊ፣***

***መኰንን ዶያሞ (Ph. D. c.)***

## *ዋና ኤዲተሮች፣*

1) *ካፒተን ፀጋዬ አውጋቸው 28 ዓመት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ማስተር*
2) *አቶ አዳሙ ገ/አቢጋዝ*
3) *አቶ ዳንኤል ወንድይፍራው*
4) *ወ/ሮ ሰሎሜ ዳምጠ*
5) *ወ/ሮ ሕይወት ወ/የሱስ*
6) *ወ/ሮ ብሩክታዊት ተምሶን*
7) *አቶ መኰንን ከበደ*
8) *አቶ ስሳይ ሕሩይ*

***10) ወጣት ዳዊት አርዓያ***

***11) ፕሮፌሰር ዳንኤል ተፈራ (Economist) Property right.***

***12) ፕሮፌሰር ሥሳይ አሰፋ (Economist) Property right.***

*የሕግ አማካሪዎችና የሕግ ባለሙያዎች፣*

*13) ወ/ሮ አረጋሽ ገ/ጻድቅ (Lawyer)*

*14) ሰሎሞን ኃይሌ (Lawyer)*

*15) ኢያሱ ለገሰ (Lawyer)*

*16) ዶ/ር መሃሪ ፍሰሐ (Lawyer)*

*17) ከኢትዮ ጀርመን ሕብረት፣ አቶ ሆሄተብርሃን ጌቱ*

*18) እንጂነየር መሰፍን ደሬረ*

*19) ወ/ሮ ጽጌረዳ ሙሉጌታ ናቸው ።*